# ትምህርት አሥራ አራት

## አንደኛ ቀን　　　የፊልሞና መግቢያ

ቤተልሔም ያደገችው ክርስቲያን ባልሆኑ ቤተሰቦች ዘንድ ነበር። አባቷ ሰካራም በመሆናቸውና እናቷም ቅስም ሰባሪ ቃላት ስለሚሰነዝሩባት፥ በ14 ዓመቷ የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ጠፍታ መጣች። አዲስ አበባ ደርሳ ከአውቶቡስ ስትወርድ ዙሪያዋን የከበቡትን ጸጉረ ልውጥ ሰዎች ተመልክታ ፈራች። ለአያሌ ቀናት በጎዳናዎች ላይ ላይ ታች እያለች ሥራ ስትፈልግ ቆየች። የኋላ ኋላ አንዲት አሮጊት ሴትዮ ከሆቴላቸው ውስጥ እንድትሠራ ቀጠሯት። ነገር ግን ክፍያው በጣም አነስተኛ በመሆኑ ልብስ ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ልታገኝ አልቻለችም። አንድ ቀን የሆቴሉ ባለቤት የሆኑት አሮጊት ወደ ሆቴሉ ከሚመጡት እንግዶች ጋር አብራ ብትተኛ የተሻለ ገንዘብ ልታገኝ እንደምትችል ነገሯት። ይህን አሳብ ካልተቀበለች ደግሞ ከሥራ እንደሚያባርሯት አስጠነቀቋት። በመሆኑም በ14 ዓመት ዕድሜዋ ቤተልሔም ሴተኛ አዳሪ ሆነች። በዚህ ጊዜ ሕይወት መረራት። የሚተኟት ወንዶች አለአግባብ ያንገላቷት ነበር። ብዙውን ጊዜ ከተኟት በኋላ ገንዘብ አይሰጧትም። ከምታገኘውም ገንዘብ አብዛኛውን የሆቴሉ ባለቤት ይወስዱባታል። አንድ ቀን ሁኔታው በጣም ስለመረራት ራሷን ለመግደል ወሰነች። ራሷን ስለምታጠፋበት መንገድ እያሰላሰለች ስትሄድ ከአንዲት ትንሽ ቤት የሙዚቃ ድምጽ ተሰማት። ይህ በሆቴሉ ውስጥ ሁልጊዜ ከምትሰማው ሙዚቃ የተለየ በመሆኑ፥ ቀረብ ብላ ከግቢው ጥግ በመቀመጥ ታዳምጥ ጀመር። የቤቱ ባለቤት ቤተልሔምን ተመልክታ ቀረብ አለችና ስለ ክርስቶስ ወንጌል መሰከረችላት። በዚህ ጊዜ እርሷን ከመውደዱ የተነሣ ሕይወቱን ሊሰጥ የፈቀደ ሰው በመኖሩ እጅግ ተደነቀች። እግዚአብሔር ኃጢአቷን ይቅር ለማለትና አዲስ ሕይወት ለመስጠት በመቻሉ ልቧ ራደ። በተሰበረ ልብ እንባዋን እያፈሰሰች ክርስቶስን የግል አዳኟ አድርጋ አመነች።

> 1ኛ ጥያቄ፡- ሉቃስ 5፡29-32 አንብብ። ክርስቶስ እንደ ሐኪም ሁሉ መንፈሳዊ በሽተኞች የሆኑትን ሰዎች ለመፈወስ እንደ መጣ ተናግሯል። ሀ) እግዚአብሔር እንደ ቤተልሔም ዓይነቷን ልጅ የመረጠው ለምን ይመስልሃል? ለ) እግዚአብሔር እንደ ቤተልሔም ያሉትን ሰዎች የሚወድና የሚያድን ከሆነ፥ ብዙ ክርስቲያኖች ማኅበረሰቡ ለሚንቃቸው ሰዎች ወንጌሉን ለመመስከር የማይፈልጉት ለምንድን ነው? ሐ) ማኅበረሰቡ ካገለላቸው ሰዎች ጋር ለመተባበር አለመፍቀዳችን ስለ ልባችን፥ ስለ ራሳችን፥ ስለ ኃጢአትና ስለ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ግንዛቤ እንዳለን ያሳያል? ይህ በሉቃስ 5፡29-32 ለተገለጸው የክርስቶስ አመለካከት የሚለየው እንዴት ነው?

የፊልሞና መጽሐፍ እግዚአብሔር አንድን ባርያ በማዳን ያሳየውን አስደናቂ ጸጋ ይናገራል። አናሲሞስ የተባለ ባርያ ከቆላስይስ ኮብልሎ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ተጉዞ ወደ ሮም ሄደ። ኑሮው በፍርሃት የተሞላ መሆኑ አያጠራጥርም። ባለሥልጣናት ቢያገኙት፥ ሊገደል ይችል ነበር። እሚኖርበት ቤትና ስፍራ ስላልነበረው፥ ምናልባትም ለምኖ እየበላ በጎዳናዎች ላይ ሳያድር አልቀረም። እግዚአብሔር ግን ይህን ባርያ አሰበው።

በሚያስገርም ሁኔታ እግዚአብሔር አናሲሞስን ወደ ጳውሎስ መራው። አናሲሞስ የክርስቶስን ወንጌል በሰማ ጊዜ በክርስቶስ አዳኝነት አመነ። በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አናሲሞስ በመንፈሱ ነፃ ሆነ። እንግዲህ አሁን ምን ማድረግ አለበት? ጳውሎስ አናሲሞስን ፊልሞና ወደሚባለው ጌታው እንዲመለስ ግድ አለው። ፊልሞና ነጻነቱን ቢሰጠው መልካም ይሆናል። ነገር ግን ለአናሲሞስ ከጌታው በመኮብለል ነጻነቱን ማግኘቱ ተገቢ አልነበረም። በመሆኑም ጳውሎስ አጭር ደብዳቤ ለፊልሞና ጽፎ አናሲሞስን ወደ ጌታው መለሰው። ጳውሎስ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፊልሞና አናሲሞስን በክርስቶስ ወንድሙ አድርጎ እንዲቀበለውና በጥሩ ሁኔታ እንዲያስተናግደው ይጠይቀዋል። መንፈስ ቅዱስ ዝቅተኛ ለሆነው ባሪያ እግዚአብሔር ያሳየውን ፍቅር ለማመልከትና ሰዎች ከክርስቶስ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት ምንም ዓይነት ጥፋት ቢፈጽሙ የእግዚአብሔር ቤተሰብ በጸጋ፥ በይቅርታና በአቀባበል የተሞላ እንዲሆን ሁላችንንም ለማስተማር ይችን አጭር ደብዳቤ ጠብቋታል።

> 2ኛ ጥያቄ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ ፊልሞና አንብብ። ስለ ደራሲው፥ ፊልሞና ማን እንደ ነበረ፥ አናሲሞስ ማን እንደ ነበረና የመልእክቱ ዓላማ ምን እንደሆነ ጠቅለል አድርገህ ግለጽ።

## የፊልሞና ደራሲ

> 3ኛ ጥያቄ፡- ፊልሞና 1ን አንብብ። ሀ) ደራሲው ማን ነው? ራሱን እንዴት ገለጸው? ይህ በቲቶ መልእክት ውስጥ ራሱን ከገለጸበት ሁኔታ የሚለየው እንዴት ነው? ለ) መልእክቱ የተጻፈው ለማን ነው?

የፊልሞና መልእክት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከምናገኛቸው የጳውሎስ መልእክቶች በጣም አጭሩ ነው (ይህ መልእክት አንድ ምዕራፍ ብቻ ስላለው የፊልሞናን መልእክት በምንጠቅስበት ጊዜ ምዕራፉን ትተን ቁጥሩን ብቻ እንጽፋለን።) የፊልሞና መልእክት አጭርና በባህሪውም ግላዊ መልእክት ያዘለ መሆኑ፥ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከጳውሎስ መልእክቶች የመጨረሻው አድርገው አስቀምጠውታል። በጊዜ ቅደም ተከተል ይህ መልእክት የተጻፈው ሦስቱ የእስር ቤት መልእክቶች፥ ማለትም የኤፌሶን፥ የፊልጵስዩስ፥ የቆላስይስ መእክቶች በተጻፉበት ወቅት ነው። እነዚህ አራቱ መልእክቶች የተጻፉት በተመሳሳይ ጊዜ ጳውሎስ ሮም ውስጥ ታስሮ በነበረበት ወቅት ነው።

ጳውሎስ የዘመኑን የደብዳቤ አጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ በቀዳሚነት የደብዳቤው ደራሲ ራሱ መሆኑን በማስታወቅ ይጀምራል። ነገር ግን ጳውሎስ ራሱን የክርስቶስ እስረኛ በማለት በተለየ ሁኔታ ይገልጻል። በዚህ ስፍራ ሐዋርያ መሆኑን አልጠቀሰም። በሌሎች ስፍራዎች እንዳሰፈረው የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ ሲልም አልተናገረም። ጳውሎስ ራሱን እንደ እስረኛ ያስታወቀው በዚህኛው መልእክት ውስጥ ብቻ ነው። ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ ሐዋርያነቱን ያልጠቀሰው እንደ ሌሎቹ መልእክቶች ለብዙ አንባቢዎች የማይቀርብ በመሆኑ ነው። ይህ መልእክት የሚነበበው በፊልሞና ቤተሰብ ብቻ ይሆናል። በመሆኑም በሐዋርያነት ሥልጣኑ ላይ ብዙም ትኩረት

አልሰጠም። ይልቁንም ጳውሎስ ለፊልሞናና ቤተሰቡ የላከው በወዳጅነት መንፈስ የሚነበብ መልእክት ነበር። ጳውሎስ ስለመታሰሩ የገለጸው ስለ ወንጌሉ እየከፈለ ያለውን ዋጋ ለፊልሞና ለመግለጽ ነበር። በዚህም ውስጥ ፊልሞና በኮበለለው ባሪያው በአናሲሞስ በኩል ምን ያህል እንዳጽናናው መግለጽ ይፈልጋል።

## ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ለማን ነበር?

ጳውሎስ ይህን መልእክት፥ «ለተወደደውና አብሮን ለሚሠራ ለፊልሞና፥ ለእኅታችንም ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥ በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን» እንደላከ ይናገራል። ፊልሞናና አፍብያ ምናልባትም የኮበለለው ባሪያ የአናሲሞስ ጌቶችና ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም። አርክጳ ፊልሞና የነበራት የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። አንዳንዶቹ አርክጳ የፊልሞናና የአፍብያ ልጅ ነበር ይላሉ።

ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሄዶ እንደማያውቅ ታስታውሳላችሁ። ስለሆነም ከፊልሞናና ከአፍብያ ጋር የነበረው ግንኙነት ምናልባትም ስለዚሁ ቤተሰብ በሰማው መረጃ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። ወይም ጳውሎስ በኤፌሶን በሚያገለግልበት ወቅት ከፊልሞና ጋር ተገናኝቶ ይሆናል (የሐዋ. 19)። ጳውሎስ ምናልባትም ደግሞ ከአርክጳ ጋር በኤፌሶን ተገናኝቶ የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን እንዲያንጽ ሾሞት ይሆናል።

ስለ ፊልሞናና አፍብያ ብዙም የምናውቀው ነገር የለም። እነዚህ ሰዎች በቆላስይስ ከተማ የሚኖሩ አማኞች ነበሩ። ምናልባትም በክርስቶስ ያመኑት ጳውሎስ በሦስተኛው የወንጌል መእልክተኝነት ጉዞው ኤፌሶን ውስጥ በሚያገለግልበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ በሆነ መንገድ ለፊልሞና ደኅንነት አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ይናገራል (ፊልሞና 19)። ምናልባትም ፊልሞና ሀብታም ነጋዴ ሳይሆን አይቀርም። ይህንንም የምናውቀው በሁለት ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ፥ ባሪያ ነበረው። ይህ ድሆች ሊያደርጉት የማይችሉት ነገር ነው። ሁለተኛ፥ በቆላስይስ አማኞች የሚሰባሰቡበት ትልቅ ቤት ነበረው።

## ፊልሞና የተጻፈበት ጊዜና ስፍራ

ጳውሎስ ይህን መልእክት በጻፈበት ወቅት በሮም ታስሮ እንደነበር ግልጽ ነው። ግን ይሄ የትኛው እስራቱ እንደነበር ጳውሎስ በግልጽ አይናገርም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ጳውሎስ በኤፌሶን እንደታሰረ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ በቂሳሪያ ታስሮ ነበር ይላሉ። ይሁንና ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት ስፍራዎች የታሰረ አይመስልም። (የእስር ቤት መልእክቶች ስለተጻፉበት ጊዜ የቀረበውን መግቢያ በኤፌሶንና በፊልጵስዩስ መልእክት አንብብ።) በአመዛኙ ተቀባይነት ያለው አመለካከት ጳውሎስ በሮም ከተማ ታስሮ እንደነበር የሚያስረዳው ነው። ስለሆነም ይህ ፊልሞና መልእክት የተጻፈው የሐዋርያት ሥራ 28 እንደሚገልጸው ሳይሆን አይቀርም።

ፊልሞና የቆላስይስ መልእክት በተጻፈበት ጊዜ ነበር የተጻፈው። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ፥ መልእክቱ የተጻፈው በ60 ዓ.ም አካባቢ ይሆናል። በቆላስይስ

4፡7-9 ጳውሎስ ቲኪቆስና አናሲሞስ መልእክቱን ወደ ቆላስይስ እንደሚያመጡ ይናገራል። በመሆኑም የቆላስይስና የፊልሞና መልእክቶች የተላኩት በእነዚህ ሁለት ሰዎች አማካኝነት እንደነበር እንገነዘባለን። ይኸው አክርጳ የተባለው ሽማግሌ በቆላስይስ ስሙ ተጠቅሷል (ቆላ. 4፡17)።

## የፊልሞና ዓላማ

የመጀመሪያ ዓላማ፡ ፊልሞና የኮበለለ ባሪያውን አናሲሞስን እንዲቀበል ለማግባባት። በሆነ ምክንያት ባሪያው አናሲሞስ ከፊልሞና ኮብልሎ ነበር። ምናልባትም የሆነ ነገር ሰርቆ ሊሆን ይችላል የኮበለለው። አናሲሞስ ነጻነቱን ፍለጋ ብዙ ርቀት ተጉዞ ወደ ሮም ሄደ። ሮም ከአንድ ሚሊዮን የሚበዛ ሕዝብ የነበረባት በመሆኗ በቀላሉ ሊደበቅባት ይችል ነበር። በጥንት ዘመን፥ ከጌቶቻቸው የኮበለሉ ባሮች በጭካኔ ይቀጡ ነበር። ድንገት ቢያዙ በጋለ ብረት የማን ንብረት መሆናቸውን የሚያመለክት ምልክት ሰውነታቸው ላይ ይደረግ ነበር። በተጨማሪም በእሳት ይቃጠሉ፥ አንገታቸው ይቀላ ወይም ይገደሉ ነበር። ይህ ጭካኔ የተሞላበት ቅጣት የሚፈጸመው ሌሎች ባሪያዎች እንዳይኮበልሉ ለማስጠንቀቅ ነበር። እግዚአብሔር አናሲሞስን ወደ ጳውሎስ በመምራቱ ወንጌልን ሊሰማ ችሏል። አናሲሞስ በወንጌል አምኖ ከዳነ በኋላ ለአጭር ጊዜ አስረኛውን ጳውሎስን ሲረዳው ቆየ (የሐዋ. 28፡17-31 አንብብ።) አናሲሞስ የተመለሰው በጳውሎስ ገፋፊነት ወይም ራሱ አናሲሞስ ወደ ጌታውና አሁን ደግሞ በክርስቶስ ወንድሙ ወደ ሆነው ፊልሞና ተመልሶ ራሱን ማስገዛት እንዳለበት በመገንዘቡ ይሆን የምናውቀው ነገር የለም። በሮም ሕግ መሠረት፥ ጳውሎስ አናሲሞስን ወደ ጌታው የመመለስ ግዴታ ነበረበት። ጳውሎስ ፊልሞና በዘመኑ ልምድ አናሲሞስን በሞት እንዳስቀጣውና ዳሩ ግን እንደ ክርስቲያን ወንድም እንዲቀጥረው በመጠየቅ ይህን ደብዳቤ ላከለት። አንዳንድ ምሁራን ጳውሎስ ፊልሞና ለወንጌል መልእክተኝነት አገልግሎቱ ይረዳው ዘንድ አናሲሞስን መልሶ እንዲልክለት እየጠየቀው ነበር ይላሉ (ፊልሞና 14)። ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ በፊልሞና 21 ላይ «ከምልህ ይልቅ አብልጠህ እንድታደርግ አውቄ» ሲል፥ ፊልሞና አናሲሞስን ነፃ እንዲያወጣው መጠየቁ ነው ይላሉ። በዚህ ጊዜ ሁለቱም በክርስቶስ አንድ ናቸውና። ይህ አጭር መልእክት በአዲስ ኪዳን ውስጥ መካተቱ፥ ምናልባትም ፊልሞና እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በእኩል ደረጃ እንደሚወድና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሪያዎችና ነፃ ሰዎችም እኩል መሆናቸውን እንደተገነዘበ ያመለክታል። ምናልባትም አናሲሞስ ነፃ ወጥቶ ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛ ዓላማ፡- ጳውሎስ በቅርቡ ተፈትቶ ወደ ቆላስይስ ለመምጣት እንደሚፈልግ ለፊልሞና ለመግለጽ ነው። ጳውሎስ በፊልሞና ቤት ውስጥ ማረፍ ይችል እንደሆነም ጠይቋል። ጳውሎስ በአካባቢው የአገልግሎት ጣቢያ አድርጎ ሊጠቀምበት የሚችለውን ልዩ የእንግዳ ክፍል እንዲያዘጋጅለት ይፈልጋል።

ሦስተኛ ዓላማ፡- ሌሎች ክርስቲያን ባሪያ አሳዳሪዎች ባሪያዎቻቸውን፥ በተለይም ክርስቲያን ባሪያዎቻቸውን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ለመምከር። በዚያን ዘመን በሮም ከተማ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች

ግማሾቹ፥ በአቴና ከነበሩት ደግሞ ሦስት አራተኛዎቹ ባሪያዎች እንደነበሩ ይገመታል። ይህም በመጀመሪያው ምእተ ዓመት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ባሮች እንደነበሩ ያመለክታል። እነዚህ ባሮች ምንም ዓይነት መብት ያልነበራቸውና እንደ ንብረት የሚቆጠሩ ነበሩ። ከእነዚህ ባሪያዎች ብዙዎቹ በክርስቶስ አምነው ነበር።

እንዲያውም በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የባሪያዎች ቁጥር ከነፃ ሰዎች ይበልጥ ነበር። ወንጌሉ እየተስፋፋ ሲሄድ፥ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ክፉ ልምምድ (ባሪያ ፍንገላ) ምን ማድረግ እንዳለባት መወሰን ነበረባት። ክርስቲያን የባሪያ አሳዳሪዎችና ክርስቲያን ባሪያዎች ክርስቶስ ከእነርሱ የሚጠብቀው ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋቸው ነበር። አዲስ ኪዳን ይህንን ክፉ የባሪያ ፍንገላ ልምምድ በግልጽ ሲቃወም አንመለከትም። ባሪያዎች እንዲያምጹ ወይም እንዲኮበልሉ አይመክርም። ባሪያ አሳዳሪዎችም ባሪያዎቻቸውን ነፃ እንዲያወጡ አይጠይቅም። ችሎቶች ወይም የፖለቲካ አስተዳደሮች ለዚህ ችግር መፍትሔ እንዲፈልጉ አላሰቡም።

ልክ ውኃ ቀስ ብሎ ልብሳችንን እንደሚያጸዳ ሁሉ፥ አዲስ ኪዳንም የባርነትን መጥፎነት በርጋታ ያሳያል። በዚህም ረገድ አያሌ ነጥቦች ተጠቅሰው እንመለከታለን። በመጀመሪያ፥ አዲስ ኪዳን ባሪያዎች እንስሳት ሳይሆኑ፥ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች መሆናቸውን ያስረዳል። ሁለተኛ፥ በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ሰዎች በምድር ላይ ባሪያዎች ይሁኑም አይሁኑም እኩል መሆናቸውን ያስረዳል። ሦስተኛ፥ እንደ ጳውሎስ ያሉ ጸሐፊዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የባሪያዎቹ ጌቶችና ባሪያዎች አንድ መሆናቸውን ይገልጻሉ። ባሪያ ወይም ጨዋ የሚባል ነገር የለም (ገላ. 3፡28)። ይህም አንዱ አስፈላጊ ሌላው የተናቀ ተደርጎ የሚቆጠርበት ሁኔታ እንደሌለ ያመለክታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለው ከእንዲህ ዓይነቱ አንድነት የተነሣ ጳውሎስ አናሲሞስ ከእንግዲህ ባሪያ ብቻ ሳይሆን በጌታ ወንድም መሆኑን ገልጾአል (ፊልሞና 16)። ይህ ባሪያዎች ጌቶቻቸው የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ናቸው ብሎ የሚያስበውን የባሪያ አሳዳሪነት ሥርዓት ከመሠረቱ አናግቷል። በመሆኑም፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በባሪያዎችና በጌቶቻቸው መካከል ፍጹም አዲስ ግንኙነት መመሥረቱ አስፈላጊ ነበር። አራተኛ፥ ጳውሎስ የባሪያ አሳዳሪዎች ባሪያዎቻቸውን በፍትሕ እንዲያስተዳድሩ ይጠይቃል። ምክንያቱም እርሱ በርሳችን ፍትሕ የሰፈነበት ግንኙነት እንዲኖረን በሚጠይቀው በእግዚአብሔር ፊት አድልዎ የለምና (ቆላ. 4፡1፥ ኤፌ. 6፡9)። አምስተኛ፥ ጳውሎስ ክርስቲያን ባሪያዎች ነፃ ለመውጣት እንዳይታገሉና ወንጌሉን በሚያስከብር መንገድ አገልግሎታቸውን እንዲያበረክቱ ጠይቋል (ቆላ. 3፡22-25)።

ምናልባትም ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የፊልሞና መልእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲያስቀምጡ ያደረጋቸው በባርነት ላይ የተሰጠው ይህ ደጎንነትን የሚያንጸባርቅ ትምህርት ሳይሆን አይቀርም።

አራተኛ ዓላማ፡- ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰቡ ላገለላቸው ሰዎች መራራት እንዳለባት ለማሳየት። ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በአብዛኛው

የኃጢአተኞች፥ የቀራጮችና የአመንዝራዎች ወዳጅ በመሆኑ ምክንያት ወቀሳ ይሰነዘርበት ነበር (ማቴ. 11፡19)። እነዚህ ማኅበረሰቡ ያገለላቸው ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው የሚያመለክተውን ወንጌል መስማት ያስፈልጋቸው ነበር። ሁሉም በእኩልና ተወዳጅ ወደሚሆኑበት የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብነት መምጣት ያስፈልጋቸው ነበር።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ማኅበረሰቡ የሚያገልላቸውን ቡድኖች ዘርዝር። ለ) ክርስቶስ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢኖር ኖሮ ከእነዚህ የሕዝብ ቡድኖች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት የሚያደርግ ይመስልሃል? እንዴት የሚያስተናግዳቸው ይመስልሃል? ሐ) ክርስቶስ ሕዝቡ (ቤተ ክርስቲያን) እነዚህን ሰዎች እንዴት እንዲያስተናግዱ የሚፈልግ ይመስልሃል? መ) ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሰዎች ያስተናገደበትን ሁኔታ ክርስቶስ እንድናስተናግዳቸው ከሚፈልገው መንገድ ጋር አነጻጽር። ይበልጥ ክርስቶስ የሚፈልገውን ለማድረግ እንደሚችል ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ግንዛቤ ልምምድ ውስጥ ሊከሰቱ የሚገባቸው ለውጦች ምን ምንድን ናቸው?

## የፊልሞና ልዩ ባሕርያት

1. በዚህ መልእክት ውስጥ ዐቢይ አስተምህሮ ወይም የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ አልተነሣም። ነገር ግን ፊልሞና የግል ጉዳይ የሚመስለውን አጀንዳ ሲያንጸባርቅ እንመለከታለን። ይህም ቀደም ሲል የኮበለለውንና አሁን ወደ ጌታው የሚመለሰውን ባሪያ የሚመለከት ነበር።

2. ፊልሞና ጳውሎስ የኮበለለውን ባሪያ በሚመለከተው አስቸጋሪ ጉዳይ ውስጥ በምን እጁን እንዳስገባ ሊጠይቅ ስለሚችል፥ ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው በጥንቃቄና በዘዴ ነበር። ጳውሎስ ፊልሞናን ሳያስቀይም ጥያቄውን ለማቅረብ ይፈልጋል። ምሁራን ጳውሎስን ጥንታዊ የግሪክና የሮም ጸሐፊዎች የሚከተሉትን የደብዳቤ አጻጻፍ እንደተከተለ ያስባሉ። ከፊልሞና ጋር ግንኙነት ለመመሥረት በመሻት ደብዳቤውን ሲጀምር እንመለከታለን (ፊልሞና 4-10)። ከዚያ በኋላ ፊልሞና ለአናሲሞስ የነበረውን አመለካከት ለመቀየር ይሞክራል (ፊልሞና 11፡19)። ከዚያም የፊልሞናን ልብ ለመንካት ይፈልጋል (ፊልሞና 20-21)። በዚህ ዓይነት ጳውሎስ ፊልሞና እግዚአብሔር ለአናሲሞስ እንዲያደርግ የፈለገውን ለማድረግ ወደሚችልበት ደረጃ ሲመራው እንመለከታለን።

3. ጳውሎስ መልእክቱን ለፊልሞና ለማስተላለፍ የቃላት ጨዋታን ይጠቀማል። የአናሲሞስ የስሙ ትርጉም ጠቃሚ ማለት ነው። ጳውሎስ በመንፈሳዊ አነጋገር ያልዳነና የኮበለለ ባሪያ በመሆኑ አናሲሞስ ቀደም ሲል ለፊልሞና እንዳልጠቀመ ይናገራል። አሁን ግን ወደ ጌታው ስለተመለሰና ከሁሉም በላይ የፊልሞና መንፈሳዊ ወንድም በመሆኑ፥ አናሲሞስ ጠቃሚ ሰው ሆኖ መገኘቱን ያስረዳል (ፊልሞና 11)።

## የፊልሞና አስተዋጽኦ

1. መግቢያና ሰላምታ (ፊልሞና 1-7)
2. ጳውሎስ ፊልሞና አናሲሞስን ፍቅር ብሎ እንዲቀበለው ይጠይቀዋል (ፊልሞና 8-22)።
3. የማጠቃለያ አሳቦች (ፊልሞና 23-25)

5ኛ ጥያቄ፡- ፊልሞናን አንብብ። ዛሬ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ሊያስተላለፍ የፈለጋቸው አንዳንድ ጠቃሚ እውነቶች ምን ምንድን ናቸው?

## መግቢያና ሰላምታ (ፊልሞና 1-7)

ከቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን አስገራሚ ባሕርያት አንዱ በአማኞች መካከል የነበረው ፍቅርና መተሳሰብ ነበር። በተራራቁ ስፍራዎች የነበሩት ብዙም የማይታወቁ አማኞች ሳይቀር ከልባቸው ይዋደዱ ነበር። ጳውሎስ የሚኖረው ሮም ውስጥ ሲሆን ፊልሞና ደግሞ በቆላስይስ ውስጥ ይኖር ነበር። ይህም በመካከላቸው ከ1200 ኪሎ ሜትሮች በላይ ርቀት መኖሩን ያመለክታል። ጳውሎስ ቀደም ብሎም ከፊልሞና ጋር አብሮ ያሳለፈ አይመስልም። ይሁንና ለፊልሞና የጻፈው መልእክት ጥልቅ የወዳጅነት መንፈስ የሚታይበት ነበር። በተጨማሪም ጳውሎስ በቀላሉ የሰውን ስሜት ሊነኩ ስለሚችሉ አንዳንድ ጉዳዮች የፊልሞናን እርዳታ ለመጠየቅ ሲደፍር እንመለከታለን። ጳውሎስ አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካላት ናቸው የሚለውን እውነት ተግባራዊ እያደረገ ነበር። በመሆኑም፥ ጣልቃ እንደገባን ወይም ሌላውን ሰው ለራሳችን ዓላማ እንደተጠቀምንበት ሳናስብ ከክርስቲያን ወገኖች እርዳታ ልንጠይቅና አንዳችን ለሌላችን ልንጸልይ እንደምንችል ከዚህ መልእክት ውስጥ መረዳት ይቻላል።

ጳውሎስ ይህንን አጭር መልእክት የጻፈው ለፊልሞና፥ ለአፍብያ (ምናልባትም የፊልሞና ባለቤት) እና አርክጳ ነበር። አንዳንድ ሰዎች አርክጳ የፊልሞና ልጅና በፊልሞና ቤት ውስጥ የምትሰባሰብ ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደነበረ ያስባሉ።

ጳውሎስ እስረኛ የነበረ ቢሆንም፥ ከእስረኛነቱ ችግሮች ባሻገር ስለ ሌሎች ያስብ ነበር። ጸሎቶቹ ያተኮሩት በግል ራሱ ስለሚባረክበት መንገድ አልነበረም። ይልቁንም ጳውሎስ ለሌሎቹ ሲማልድ እንመለከታለን። ጳውሎስ ስለ ፊልሞናና ስለ ቤተሰቡ ለእግዚአብሔር እንደሚጸልይ ይናገራል። ጳውሎስ ፊልሞና በክርስቶስ ላይ ጠንካራ እምነት እንደነበረውና ቅዱሳንን ሁሉ እንደሚወድ በመስማቱ፥ ጸሎቱ በምስጋና የተሞላ ነበር። ፊልሞና የራሱን ቤተሰብ፥ የራሱን ጎሳ ወይም የራሱን ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚወድ ሰው አልነበረም። ፊልሞና አማኞችን ሁሉ በመውደዱ የታወቀ ሰው ነበር። ጳውሎስ የፊልሞና ፍቅር እንደ ንጹሕ የምንጭ ውኃ እንደነበር ይናገራል። ይህም ፊልሞና የሚያጋጥመውን ሰው ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያነቃቃ መልካም አገልጋይ እንደነበረ ያመለክታል።

6ኛ ጥያቄ፡- ከፍቅራቸው ትኩስነት የተነሣ ሌሎችን አማኞች የሚያነቃቁትን ክርስቲያኖች አይተህ ታውቃለህ? እንዲህ ዓይነቱ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈለገው ለምንድን ነው? አንድ ሰው ለሌሎች የዚህ ዓይነት ፍቅር እንዲኖረው ምን ማድረግ ይኖርበታል?

ጳውሎስ ከምስጋናው በተጨማሪ ፊልሞና በክርስቶስ ላይ ያለውን እምነት ለሌሎች በድፍረት ማካፈል እንዲችል ይጸልይለታል። ጳውሎስ

«ከእኛ ዘንድ ያለውን በጎ ነገር ሁሉ በማወቅ» የሚለውን አሳብ ከምስክርነት ጋር ማያያዙ አስገራሚ ነው። እምነታችንን ለሌሎች በምናካፍልበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ያለን እውቀት እንዲያድግ ይረዳናል። እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን ልዩ ዕድሎች እንዳሉን እንድንረዳ ያስችለናል።

## ጳውሎስ ፊልሞና አናሲሞስን ይቅር እንዲለውና እንዲቀበለው ይጠይቀዋል (ፊልሞና 8-22)

ጳውሎስ እዚህ ላይ የመልእክቱን ዓላማ ያብራራል። ጳውሎስ ፊልሞና አናሲሞስ ወደ እርሱ በሚመለስበት ጊዜ በፍቅር እንዲቀበለው ይለምነዋል። የስሙ ትርጉም «ጠቃሚ» የሆነው አናሲሞስ ቀደም ሲል ከፊልሞና በመኮብለሉ ሳይጠቅመው ቀርቶ ነበር። አሁን ግን አናሲሞስ የተለወጠና እንደ ፊልሞና በክርስቶስ የሚያምን ሰው ሆኖ ስለሚመለስ ለፊልሞናም ሆነ ለጳውሎስ «ጠቃሚ» ነበር። ጳውሎስ አናሲሞስን «ልጄ» ይለዋል። ይህም ምናልባትም ጳውሎስ አናሲሞስን ወደ ጌታ እንዳመጣውና አብረው በቆዩባቸው ጊዜያት በጣም ተዋድደው እንደ ነበር ያሳያል።

አናሲሞስ በክርስቶስ ካመነ በኋላ እስረኛ የነበረውን ጳውሎስን ሲያገለግለው ቆይቷል። በመሆኑም እዚያ ቆይቶ ቢረዳው ይወድ እንደ ነበር አስረድቷል። ነገር ግን ያለባለቤቱ ፈቃድ አንድን ነገር መውሰዱ ትክክል አለመሆኑን ያውቃል። ስለሆነም ጳውሎስ አናሲሞስን ወደ ፊልሞና መለሰው። ፊልሞና አናሲሞስን መልሶ ለጳውሎስ ለመስጠት ቢፈልግ ውሳኔው የራሱ ነበር። ፊልሞናም ወደ ክርስቶስ የመጣው በጳውሎስ ምስክርነት በመሆኑ የጳውሎስ ውለታ ነበረበት።

ጳውሎስ ከአናሲሞስ አሳዛኝ ሕይወት፥ ጳውሎስን በማግኘቱና በክርስቶስ በማመኑ ውስጥ የእግዚአብሔር ታላቅ እጅ እንደ ነበረበት ተገንዝቧል። የአናሲሞስን መኮብለል ጨምሮ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በሙሉ ይቆጣጠር ነበር። አሁን አናሲሞስ ለመታዘዝ የማይፈልግ ባሪያ ሆኖ አልነበረም ወደ ፊልሞና የተመለሰው። ነገር ግን በጌታ የተወደደ ወንድም ሆኖ ነበር የተመለሰው። አናሲሞስ ለጳውሎስም ሆነ ለፊልሞና የተወደደው ወንድም ነበር። ምክንያቱም አሁን ሁሉም የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናቸውና። ጳውሎስ ፊልሞናን የክርስቶስ አካል አናሲሞስ እንዲቀጣ ከሚፈቅደው የአገሪቱ ሕግ በላይ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝበዋል። አሁን በክርስቶስ ወንድሞች በመሆናቸው፥ ፊልሞና አናሲሞስን በጌታ ወንድሙ አድርጎ እንዲቀበለውና ይቅርታን እንዲያደርግለት ይጠይቀዋል።

7ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሀብታሙ ፊልሞናና ባሪያው አናሲሞስ አሁን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካላት ሆነዋል። አናሲሞስ ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ፊልሞና እንዴት ሊያስተናግደው ይገባል ትላለህ? ለ) ይህ ባህላዊውን የጌታና ባሪያ ግንኙነት እንዴት የሚያናጋው ይመስልሃል? ሐ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ማኅበረሰቡ ያገለላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘርዝር። የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አካል መሆናቸው ቀደም ሲል ይንቋቸው ከነበሩት ሰዎች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እንዴት እንደሚለውጥ ግለጽ። መ) እነዚህ የተገለሉ ሰዎች በክርስቶስ ወንድሞችና እኅቶች መሆናቸውን ለማሳየት ፍቅርህን እንዴት ትገልጽላቸዋለህ?

ለእነዚህ ሰዎች ፍቅርህንና አቀባበልህን ለማሳየት በዚህ ሳምንት ምን ልታደርግ እንደምትችል ግለጽ።

አናሲሞስ ምናልባትም ከፊልሞና ንብረት ዘርፎ ይሆናል የሄደው። ይህ በፊልሞና ልብ ውስጥ መራርነት እንዳይፈጥር ሲል ጳውሎስ በአናሲሞስ ላይ ያለውን ዕዳ ራሱ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ገለጸ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ እርቅ ይቅርታ መጠየቅን ብቻ ሳይሆን ከተቻለ የተሰረቀውን ንብረት መመለስን ወይም በሌላው ሰው ላይ የፈጸምነውን ጥፋት ማስተካከል ይጨምራል። ጳውሎስ በአናሲሞስ ምትክ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ጳውሎስ አናሲሞስ የሰረቀውን ንብረት ዋጋ ለመክፈል የፈለገው ለምን ይመስልሃል? ለ) ይህ ይቅርታ በምንጠይቅበት ጊዜ በተግባራችን ወይም ያጠፋነውን በማስተካከል ልንፈጽመው ስለሚገባው ተግባር ምን ያስተምረናል? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ከሰረቁት ገንዘብ ይቅርታ ከጠየቁ ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ እንደሌለባቸው የሚያስቡት ለምንድን ነው? ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይመስልሃል? ለምን?

ጳውሎስ በቅርቡ ከእስር ቤት እንደሚወጣ ያስባል። በዚህም ጊዜ በቆላስይስና ሎዶቅያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እያገለገለ የተወሰነ ጊዜ ለመቆየት ዐቅዷል። ስለሆነም ጳውሎስ ፊልሞና በቤቱ ውስጥ እንዲቆይ ይፈቅድለት ዘንድ ይጠይቀዋል። ጳውሎስ ለብቻው የእንግዳ ክፍል ተዘጋጅቶለት ለመቆየት ይፈልጋል።

## የመዝጊያ አሳቦች (ፊልሞና 23-25)

9ኛ ጥያቄ፡- ቆላ. 4፡12-14 አንብብ። የቆላስይስና የፊልሞና መልእክቶች አጨራረስ ተመሳሳይ የሚሆነው እንዴት ነው? በሁለቱም መልእክቶች ውስጥ የተጠቀሱትን ስሞች ዘርዝር።

ጳውሎስ የኤጳፍራን ሰላምታ በማቅረብ ይህንን ደብዳቤ ይደመድማል። ኤጳፍራ የቆላስይስ ክርስቲያኖች በሚገባ የሚያውቁትና በዚህ ጊዜ ከጳውሎስ ጋር ታስሮ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። ጳውሎስ በተጨማሪም የማርቆስን፥ የአርስጥሮኮስን፥ የዴማስና የሉቃስንም ሰላምታ አስተላልፎአል። እነዚህ ሁሉ ስሞች በቆላስይስም መልእክት ውስጥ ይገኛሉ። ይህም ሁለቱም መልእክቶች በተመሳሳይ ጊዜ መጻፋቸውን ያመለክታል።

10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ማኅበረሰቡ ላገለላቸው ሰዎች ስለሚኖረን አመለካከት ከፊልሞና መልእክት ምን እንማራለን? ለ) ማኅበረሰቡ ካገለላቸው ሰዎች፥ በተለይም ከክርስቲያኖች ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት እግዚአብሔር ከእኛ ምን ይጠብቃል?

## ሁለተኛ ቀን የዕብራውያን መግቢያ

ተክሌ ተወልዶ ያደገው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። ወላጆቹ የኦርቶዶክስ አማኞች ነበሩ። ከልጆቻቸው አንዱ በሚታመምበት ጊዜ፥ የተክሌ ወላጆች የኦርቶዶክስ ቄስ ይጠሩ ነበር። ቄሱ ይመጣና ዶሮ በማረድ ቅዳሴ ቢጤ ያደርጋል። የዶሮውን ደም በቤቱ ውስጥ ይረጫል። ይህንንም የሚያደርገው ለልጁ መታመም ምክንያት ሆኗል ብሎ የሚያስበውን ክፉ መንፈስ ለማባረር ነበር።

አፈወርቅም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር ተወልዶ ያደገው። ምንም እንኳ ቤተሰቦቹ ሙስሊሞች ነን ቢሉም፥ ብዙም ወደ መስጊድ አይሄዱም ነበር። በቤታቸው ውስጥ ሰው በሚታመምበት ጊዜ፥ በተቀደሱ ዛፎች ውስጥ የሚኖረውን ዝነኛ ጠንቋይ ወይም ፈዋሽ ሩጠው ይጠሩት ነበር። ለጠንቋዩ ፍየል ያርዱለትና ግለሰቡ የፍየሉን ደም ከመያዙም በላይ አንጀቱን ይመረምራል። የፍየሉ አንጀት ጠንቋዩ በልጁ ላይ በሽታውን ማን እንዳመጣ እንዲያውቅ ይረዳዋል ተብሎ ይታመናል። ከዚያም ደሙን በመጠቀም፥ ጠንቋዩ የመናፍስትን ቁጣ ያረግበዋል። ከዚህ ሥርዓት በኋላ መናፍስቱ ልጁን እንደሚጠብቁትና ከበሽታ እንደሚከላከሉት ይታመናል።

11ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የኦርቶዶክስ ቄስና ጠንቋይ መሥዋዕቶችና ደም የሚጠቀሙት ለምንድን ነው? የእነዚህ መሥዋዕቶች ዓላማ ምንድን ነው? ለ) ዛሬም አንዳንድ አማኞች ቤተሰቦቻቸው ውስጥ ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ጠንቋዮችን ወይም ምትሃታዊ ኃይል እንዳላቸው የሚታመኑባቸውን ቄሶች የሚጠሩት ለምንድን ነው? ሐ) ክርስቲያኖች ፈውስ ለማግኘት ወይም ከእርግማን ለመዳን የኦርቶዶክስን ቄስ ወይም ጠንቋይን መጠቀም ያስፈልጋቸዋል? ለምን?

ከጥንት ዘመን ጀምሮ፥ ከሁሉም ባህሎች ውስጥ ማለት ይቻላል የእንስሳት መሥዋዕት የአምልኮ አካል ነበር። እግዚአብሔር የአዳምና የሔዋንን እርን ለመሸፈን እንስሳትን ከገደለበት ጊዜ አንሥቶ (ዘፍጥ. 3፡21)፥ የእንስሳት መሥዋዕቶች የአምልኮ አካል ነበሩ። ሰይጣን ሰዎች ሐሰተኛ አምልኮ እንዲያካሂዱ ለማድረግ የእንስሳት መሥዋዕትን ያበረታታል። ይህ ሐሰተኛ ልምምድ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጸውን እውነተኛ አምልኮ በመኮረጅ የሚከናወን ነው።

ለመሆኑ በእንስሳት መሥዋዕትና በአማኝ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ዛሬም መሥዋዕቶቹ አስፈላጊ ናቸው? አማኞች የእንስሳትን መሥዋዕት ያቀርቡ ዘንድ ጠንቋዮችን ወይም የተለዩ ካህናትን መጠቀማቸው ስሕተት ነውን? የዕብራውያን መጽሐፍ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምን መልስ ይሰጣል? አይሁዶች በክርስቶስ ካመኑ በኋላም ሳይቀር የእንስሳት መሥዋዕት ሥርዓታቸውን ለመቀጠል ይፈልጉ ነበር። የዕብራውያን ጸሐፊ የእንስሳትን መሥዋዕት ለኃጢአት ይቅርታ (ወይም የመናፍስትን ቁጣ ለማብረድ፥ ለፈውስ ወይም ከእርግማን ለመከላከል) መጠቀሙ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ላይ ያለንን እምነት የሚቃረን መሆኑን ያስረዳል። ሰዎች ደኅንነትን ከማግኘታቸው በፊት በእንስሳት መሥዋዕትነት፥ በካህናት ወይም በጠንቋዮች አማካኝነት የሚያገኟቸውን ነገሮች በሙሉ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ እንደፈጸመልን የዕብራውያን ጸሐፊ ያስገነዝባል።

በመሆኑም እነዚህን ጥንታዊ ሥርዓቶችና የእንስሳት መሥዋዕት መጠቀሙ ግለሰቡ በክርስቶስ ላይ ሕያው እምነት እንደሌለው ያመለክታል። የክርስቶስ ሞት ሌሎችን መሥዋዕቶች ሁሉ አላስፈላጊ አድርጓችዋል።

12ኛ ጥያቄ፦ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የዕብራውያን መልእክት ርእስ ምንድን ነው? የመጽሐፉ ደራሲ ማን ነው ይላል?

## አጠቃላይ መልእክቶች

ምንም እንኳን በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዕብራውያን መጽሐፍ ርእስ የጳውሎስን ደራሲነት ቢያሳይም፥ ይህ ርእስ በጥንታዊ መዛግብት ውስጥ አይገኝም። መጽሐፉ ራሱ በማን እንደ ተጻፈ አይናገርም። (ስለ ዕብራውያን መጽሐፍ ደራሲ በምንነጋገርበት ክፍል ስለዚሁ ጉዳይ ሰፋ አድርገን እንመለከታለን።) ስለሆነም የጥንት አማኞች የዕብራውያንን አማኞች ከጳውሎስ መልእክቶች መጨረሻና ከቀጣይ ጽሑፎች መጀመሪያ ላይ አስቀምጠውታል። ምሁራን ከዕብራውያን እስከ ይሁዳ ያለውን ክፍል «አጠቃላይ መልእክቶች» ሲሉ ይጠራሉ። አጠቃላይ መልእክቶች የተባሉበትም ምክንያት መልእክቶቹ የተጻፉት ለግለሰብ (እንደ ቲቶ) ወይም ለአንድ ቤተ ክርስቲያን (እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ) ሳይሆን፥ ለአጠቃላይ ክርስቲያኖች ወይም በዛ ላሉ ተደራሲያን በመሆኑ ነው። (ለግለሰቦች የተላኩት 2ኛ ና 3ኛ ዮሐንስ መልእክቶች ከ1ኛ ዮሐንስ ጋር አብሮ ስለሚካተቱ፥ የአጠቃላይ መልእክቶች አካላት ተደርገው ተወስደዋል።) እነዚህ ስምንት መጻሕፍት የተጻፉት በአምስት የተለያዩ ደራሲያን ነው። (ማስታወሻ፥ አጠቃላይ መልእክቶች ከዕብራውያን ሳይሆን ከ1ኛ ጴጥሮስ እንደሚጀምሩ የሚያስቡ ምሁራን አሉ።)

(ማስታወሻ፡ እነዚህ ስምንት መጻሕፍት በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀረቡበት የአቀማመጥ ቅደም ተከተል ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ይለያል። ይህም የሆነው የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስን ቅደም ተከተል ስለሚከተልና እንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ የላቲንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅደም ተከተል ስለሚከተል ነው።)

13ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ስምንቱን የአጠቃላይ መልእክቶች መጽሐፍ በቅደም ተከተል ዘርዝር። ለ) ስለ ዕብራውያን መልእክት ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። ስለ ደራሲው፥ ስለ መልእክቱ ተቀባዮችና የመጽሐፉ ዓላማ፥ ወዘተ... የቀረበውን ትምህርት ጠቅለል አድርገህ አቅርብ።

## የዕብራውያን መልእክት ደራሲ

14ኛ ጥያቄ፦ ዕብራውያን 1፡1 አንብብ። ሀ) ስለ ደራሲው የተጠቀሰ ምን ነገር አለ? ለ) ሮሜ 1፡1 አንብብ። ይህ የሮሜ መጽሐፍ ስለ ደራሲው ከሚናገረው እንዴት ይለያል?

ምንም እንኳን የዚህ መጽሐፍ የአማርኛው ርእስ «የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ዕብራውያን» ቢልም፥ ጳውሎስ የመጽሐፉ ደራሲ እንደሆነ አይናገርም። ይህ ጳውሎስ በሮሜም ሆነ በሌሎች መልእክቶቹ መግቢያ ላይ ራሱን ከሚያስታውቅበት ሁኔታ የተለየ ነው። የዕብራውያን መልእክት ደራሲ በመልእክቱ ውስጥ ስሙን አልጻፈም። ይህ ከጥንታዊ የደብዳቤ አጻጻፍ ልማድ የተለየ ነው። መልእክቱ መጀመሪያ የተጻፈላቸው ሰዎች ደራሲውን ያውቁት እንደነበረ አይጠረጠርም። ምክንያቱም ደራሲው ሊጎበኛቸው እንዳልቻለ (ዕብ. 13፡19)፥ ዳሩ ግን አንድ ቀን ከጢሞቴዎስ ጋር ለመምጣት እንደሚፈልግ ይናገራል (ዕብ. 13፡23)። እንደ አለመታደል ሆኖ፥ መጽሐፉም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የዕብራውያን መልእክት ደራሲ ማን እንደሆነ

አይናገሩም። በአጠቃላይ፥ የጥንቶቹ ምሥራቃዊያን አብያተክርስቲያናት (ሶሪያ፥ ግብጽና ኢትዮጵያ) ጳውሎስ ይህን መልእክት እንደ ጻፈ ያምናሉ። ምዕራባዊያን አብያተ ክርስቲያናት (ሮም) ግን ጳውሎስ ይህን መልእክት እንደ ጻፈ አያምኑም።

የዕብራውያንን መልእክት ቀረብ ብለን ስንመረምር፥ ስለ ደራሲው የሚከተሉትን ነገሮች እናገኛለን።

ሀ) ደራሲው የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓትና የአይሁዳዊያን ጽሑፎችን የሚያውቅ አይሁዳዊ ነበር።

ለ) ደራሲው የብሉይ ኪዳንን የግሪክ ትርጉም የሚያውቅ፥ ከፍልስጥኤም ውጭ የተወለደ ሔለናዊ አይሁድ ነበር። ደራሲው የተጠቀመበት የግሪክ ቋንቋ የፓለስታይን አይሁዶችን ዓይነት ሁለተኛ ቋንቋ አይመስልም። እንዲሁም ደግሞ የዕብራውያንን ብሉይ ኪዳን የተጠቀመው የፓለስታይን አይሁዶች በሚጠቀሙበት መንገድ አይደለም።

ሐ) ደራሲው የክርስቶስ ቀጥተኛ ደቀ መዝሙር አልነበረም። ክርስቶስን ባያየውም፥ ከክርስቶስ ጋር ከነበሩት ሰዎች ወንጌልን ሰምቷል (ዕብ. 2፡3)። (ማስታወሻ፥ ይህም ደራሲው ጳውሎስ እንዳልሆነ የሚያሳይ ይመስላል። ምክንያቱም ጳውሎስ ወንጌሉን ከክርስቶስ እንጂ ከሌሎች ሐዋርያት እንዳልተቀበለ ይናገራል። ገላ. 1፡11–12 ተመልከት።)

መ) ደራሲው በ70 ዓ.ም ቤተ መቅደሱ በሮማውያን ሲደመሰስ በሕይወት ነበር። የዕብራውያን መልእክት በተጻፈበት ወቅት፥ ቤተ መቅደሱ አገልግሎት እየሰጠ ከመሆኑም በላይ የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓትም እንደ ቀጠለ ነበር። ነገር ግን፥ በቅርብ ጊዜ ይህ ሁኔታ እንደሚያከትም የዕብራውያን መልእክት ደራሲ ገልጾአል (ዕብ. 8፡13)።

ሠ) ደራሲው ይሁዲነትን የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን፥ ሐዋርያነትና ቀደምት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተቀበሉት ዝነኛ ሰው ነበር።

ረ) ደራሲው እስር ቤት ውስጥ የነበረውን ጢሞቴዎስን ያውቅ ነበር (ዕብ. 13፡23)። የዕብራውያንን መልእክት ተቀባዮች ከጢሞቴዎስ ጋር ለመጎብኘት ይፈልግ ነበር።

ሰ) ደራሲው በአንባቢዎቹ በሚገባ ስለሚታወቅ፥ ማንነቱን ለመግለጽና ተደማጭነት ለማግኘት ስሙን መጥቀስ አላስፈለገውም።

ሸ) ደራሲው አንባቢዎቹን ለመጎብኘትና ከእነርሱ ጋር ዳግም አብሮ ለመሆን ይፈልጋል። ነገር ግን በሆነ ምክንያት (ምናልባትም እስር ቤት ውስጥ በመሆኑ) ይህን ለማድረግ ሳይችል ቀይቷል።

ለመሆኑ እነዚህን መመዘኛዎች የሚያሟላና የዕብራውያን መልእክት ደራሲ ሊሆን የሚችል ሰው ማን ነው? የተለያዩ ምሁራን የሰጧቸው አስተያየቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. ጳውሎስ፡ ከ400 ዓ.ም እስከ 1600 ዓ.ም፥ ብዙውን ጊዜ ለዚህ መጽሐፍ የተሰጠው ርእስ «የጳውሎስ መልእክት ለዕብራውያን» የሚል ነበር። ይህም የመልእክቱ ደራሲ ጳውሎስ ነው የሚል አመለካከት በስፋት እንዲታይ አድርጓል። ጳውሎስ የፈሪሳዊነት ትምህርት የተከታተለ በመሆኑ፥ የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓትንና የአይሁዶችን የአስተሳሰብ መንገዶች በጥልቀት

ሊያውቅ ይችል ነበር። ሌሎች ከላይ የቀረቡትን መመዘኛዎችንም እንዲሁ ያሟላል። የዚህ መልእክት ደራሲ ጳውሎስ ነው የሚሉ ምሁራን ጳውሎስ ስሙን ያልጠቀሰበት ምክንያት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች መጽሐፉን ለማንበብና ትምህርቶቹን ለመቀበል ፈቃደኞች እንዲሆኑ በማሰብ ነው ይላሉ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደተመለከተው፥ አይሁዶች ጳውሎስን ይጠራጠሩና ትምህርቱን ላለመቀበል ይሞክሩ ነበር። (ነገር ግን ከዕብራውያን መልእክት ውስጥ እንደምንመለከተው፥ የመልእክቱ አንባቢዎች ደራሲውን የሚያውቁት ይመስላል።) እነዚህ ምሁራን እንደሚሉት ምንም እንኳን ጳውሎስ በቀጥተኛ መገለጥ ከክርስቶስ ብዙ ነገር ቢቀበልም፥ ስለ ክርስቶስ አብዛኞቹን እውነታዎች የተማረው ከሐዋርያት ነበር ሲሉ ይከራከራሉ (1ኛ ቆሮ. 15፡1-3)። የጳውሎስ የቅርብ የሥራ ተባባሪ የሆነው ጢሞቴዎስ መጠቀሱ (ዕብ. 13፡23)፥ የዚህ መልእክት ደራሲ ጳውሎስ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ያጠነክራል።

ጳውሎስ ይህን መልእክት እንዳልጻፈው የሚናገሩ ምሁራን የሚከተሉትን ነጥቦች ይጠቅሳሉ።

ሀ) ጳውሎስ የመልእክቱ ደራሲ መሆኑን በመግቢያው ላይ አልጠቀሰም። ይህ የዕብራውያንን መልእክት ከሌሎች መልእክቶች ሁሉ ይለየዋል። አንባቢዎቹ ደራሲውን ስለሚያውቁ፥ መልእክቱን የጻፈው ጳውሎስ ቢሆን ኖሮ እንደ ሌሎች መልእክቶች ሁሉ ደራሲነቱን ይናገር ነበር።

ለ) የዕብራውያን መልእክት የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ሌሎች የጳውሎስ መልእክቶች ከተጻፉበት የተለየ ነው።

ሐ) እንደ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያሉ ጳውሎስ በተደጋጋሚ የሚጠቀምባቸው አገላለጾች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አይገኙም።

መ) ቀደምት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመጽሐፉ ደራሲ ማን እንደሆነ አያውቁም። መልእክቱ በግልጽ በጳውሎስ ቢጻፍ ኖሮ ያውቁት እንደነበር አይጠረጠርም።

2. <u>በርናባስ</u> በ200 ዓ.ም ተርቱሊያን የተባለ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ምሁር የዕብራውያን መጽሐፍ ደራሲ በርናባስ ነው ሲል ተናግሯል። በርናባስ ከላይ የተጠቀሱትን አብዛኞቹን መመዘኛዎች ያሟላል። በርናባስ ከሌዊ ወገን የተወለደ ሔለናዊ አይሁድ በመሆኑ፥ የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓትና ይሁዲነትን በሚገባ ያውቃል (የሐዋ. 4፡36)። ያደገው በፍልስጥኤም ሳይሆን ቆጵሮስ ውስጥ ነበር። አይሁዶችና የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን በርናባስን ያከብሩት ነበር። በርናባስ ከመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አንዱ አልነበረም። ነገር ግን ከሐዋርያት ጋር ጊዜ በማሳለፍ ስለ ክርስቶስ ሊያውቅ ችሏል። ምንም እንኳን በርናባስ በአሕዛብ መካከል የወንጌል ስርጭት ተግባራትን ቢያከናውንም፥ ትኩረት የሰጠው ለአይሁዶች ይመስላል።

3. አጵሎስ፡ በ15ተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ፥ ማርቲን ሉተር አጵሎስ ይህን መልእክት ሳይጽፍ እንዳልቀረ ተናግሯል። አጵሎስ በአሌክሳንደሪያ የተወለደ አይሁዳዊ ቢሆንም፥ አይሁዳዊ ክርስቲያን ነበር። አጵሎስ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለይም በአሕዛብ ዘንድ በስፋት ይታወቅ ነበር። ከአይሁዶች ጋር በመከራከር የክርስቶስን መሢህነት ለማሳየት የቻለ ብቃት ያለው አገልጋይ ነበር (የሐዋ. 18፡24-28)። ይህ ደራሲ ብሉይ ኪዳንን የተረዳባቸው አንዳንድ መንገዶች በዚህ ጊዜ በኤሌክሳንደሪያ (ግብጽ) የነበሩ አይሁዶች ከሚጽፉበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነበር።

4. ሉቃስ፡ አንዳንድ ምሁራን የዚህ መእልክት ደራሲ ሉቃስ እንደነበር ገልጸዋል። ይህንንም ያሉት ሉቃስ የጻፋቸውን የሐዋርያት ሥራና የሉቃስ ወንጌል የግሪክ ቋንቋና የአጻጻፍ ስልት ከዕብራውያን መልእክት ጋር በማነጻጸር ነው። ነገር ግን ሉቃስ አሕዛብ በመሆኑ እንዲህ ዓይነት መጽሐፍ ይጽፋል ተብሎ አይታሰብም።

5. ጵርስቅላና አቂላ፡ አንዳንድ ምሁራን ጵርስቅላ በአቂላ እገዛ ይህን መጽሐፍ እንደ ጻፈች ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች በሮም ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አይሁዶች መሆናቸውን እናውቃለን። ጵርስቅላና አቂላ ክርስቲያናዊ እውነት የማስተማር ብቃት ነበራቸው፥ ምክንያቱም ከጳውሎስ የሁለተኛና ሦስተኛ የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞዎች ላይ በከፊል የተሳተፉ ከመሆናቸውም በላይ፥ አጵሎስን ለማስተማርና ለአገልግሎት ለማዘጋጀት ከፍተኛ ከአስተዋጽኦ አድርገዋል (የሐዋ. 18፡26)። ከጳውሎስ ጋር ረጅም ጊዜ በማሳለፋቸውና ሔለናዊ አይሁዶች በመሆናቸው፥ የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓትና የግሪኩን ብሉይ ኪዳን ሊያውቁ ይችሉ ነበር። በዕብራውያን ውስጥ እንደተገለጸው የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ጉዞ በእነዚህ ሰዎች በግልጽ የሚታወቅ ነበር። ምክንያቱም ራሳቸው ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ኖረዋልና። እንዲሁም በሮም ለተወሰነ ጊዜ የቆዩ በመሆናቸው በዚያ አካባቢ ይታወቁ ነበር። ስለሆነም፥ ሰላምታ የሚልኩላቸው ጣሊያናውያን ወዳጆች ሊኖሯቸው ይችሉ ነበር። ምናልባትም ጵርስቅላ በመልእክቱ ውስጥ ስሟን ያልጠቀሰችው የሴቶች ደራሲነት በወቅቱ ተቀባይነት ስለማያገኝ ይሆናል። ይሁንና፥ ይህንን ንድፈ ሐሳብ ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል የሚያስችል ብዙ መረጃ የለንም።

ሌሎች የተለያዩ ምሁራን የሰጡአቸው የአገልጋዮች ስሞች ቢኖሩም፥ በስፋት የሚታወቁት አምስቱ እነዚህ ናቸው። መልእክቱን የጻፋት ጳውሎስ ወይም በርናባስ የነበሩ ይመስላል። ነገር ግን የዕብራውያንን መልእክት ማን እንደ ጻፈው በትክክል ለማወቅ አልተቻለም። ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዕብራውያን መልእክት ትምህርቶች አስፈላጊዎች መሆናቸውን አምነው የአዲስ ኪዳን አካል አድርገው እንዲቀበሉት አስችሏቸዋል።

## መልእክቱ የተጻፈው ለማን ነበር?

የመልእክቱ ተቀባዮች አይሁዶች መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህ የጥንት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመጽሐፉ ከሰጡት «ዕብራውያን» ከሚለው የመጽሐፉ ስያሜ በግልጽ የሚንጸባረቅ ነው። (የዕብራውያን የጥንት

የአይሁዶች ስም ነው።) መጽሐፉ አንባቢዎቹ የብሉይ ኪዳንን የመገናኛ ድንኳንና የአምልኮ ሥርዓት እንደሚያውቁም ያመለክታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉትን የአይሁዳውያን ጽሑፎችም ያውቁ ነበር።

ይሁንና፥ መጽሐፉ የተጻፈው በሮም ግዛት ውስጥ በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ አይሁዶች አይመስልም። ነገር ግን ደራሲውን ለሚያውቁና እርሱም በቅርቡ ለመጎብኘት ለሚፈልጋቸው የተወሰኑ የአይሁድ ክርስቲያኖች የተጻፈ ይመስላል። እነዚህ አንባቢዎች ስለነበሩበት ስፍራ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች ቀርበዋል። አንዳንዶች በመሥዋዕት ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ አንባቢዎቹ ቤተ መቅደሱ በነበረበትና መሥዋዕቶች በሚቀርቡበት በፓለስታይን ምድር የነበሩ መሆናቸውን ያሳያል። ሌሎች ደግሞ እነዚህ አንባቢዎች ከፓለስታይን ውጪ የነበሩ አይሁዶች መሆናቸውን ይናገራሉ። ይሁንና፥ ሁሉም አይሁዳውያን ወንዶች በዓመት ሦስት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ስላለባቸውና ሁሉም አይሁዳውያን የእንስሳት መሥዋዕቶችን ስለሚያቀርቡ፥ እነዚህ የአይሁዳውያን ማኅበረሰብ በየትኛውም ስፍራ ሊኖሩ ይችላሉ። በተጨማሪም፥ የዕብራውያን መልእክት ፓለስታይን የሚኖሩ አይሁዶች ቋንቋ በሆነው በአረማይክ ሳይሆን በግሪክ መጻፉ አይሁዶቹ ከፓለስታይን ውጭ የነበሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ይመስላል።

ብዙ ምሁራን እንደሚስማሙበት መጽሐፉ የተጻፈው በሮም ለነበሩ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ነው። ምክንያቱም ደራሲው በመጽሐፉ መጨረሻ አካባቢ ከኢጣሊያ ሰላምታ ያስተላለፉትን ሰዎች ጠቅሷል። በቀደምት ክርስቲያናዊ ጽሑፎች ውስጥ ከሁሉም በፊት የዕብራይስጥን ቋንቋ የተጠቀመው በሮም ውስጥ የነበረው ክሌመንት መሆኑ ይህን አሳብ ያጠናክረዋል። ሌሎች ደግሞ ብዙ አይሁዶች የነበሩባትን አሌክሳንደሪያን አጭተዋታል።

ከሐዋርያት ሥራና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው፥ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን ዓመታት ለአይሁዳውያን ክርስቲያኖች በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። ከ10-20 ዓመታት ለነበሩት የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ዓመታት፥ ክርስትና በዋናነት የአይሁዶች ሃይማኖት ነበር። እነዚህ አይሁዶች የወትሮው የአምልኮ ሥርዐታቸውን ብዙም ሳይለውጡ ክርስቶስ ለኃጢአታቸው የሞተ መሢሐቸው መሆኑን አምነዋል። ነገር ግን አሁንም በቤተ መቅደስ ውስጥ ቢያመልኩ (የሐዋ. 2፡46፥ 3፡1)፥ የእንስሳት መሥዋዕቶች ያቀርቡና የአይሁዶችን ባህላዊ ልምምዶች ሁሉ ይከተሉ ነበር። ከአብዛኞቹ አይሁዶች የሚለዩበት ዋናው ነገር አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በክርስቶስ መሢሕነት ማመናቸው ነበር።

ቆርኔሌዎስ ከተለወጠና የአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች በኋላ፥ ቀስ በቀስ ክርስትና እየተለወጠ ሄደ፥ ለመጀመሪያ ግዜ አሕዛብ ክርስቲያኖች ይሆኑ ጀመር። እነዚህ አሕዛብ በቤተ መቅደስ ውስጥ የማምለክ ፍላጎት አልነበራቸውም። የእንስሳት መሥዋዕቶችን ካለማቅረባቸውም በላይ፥ የአይሁዶችን ባህል አይከተሉም ነበር። የአሕዛብ አማኞች ቁጥር በጣም ጥቂት ስለነበር፥ በመጀመሪያ አይሁዳውያን አማኞች እነዚህ ወደ ክርስትና ከመጡት ጥቂት አሕዛብ ጋር ግብግብ መግጠም አላስፈለጋቸውም ነበር።

ይህ ሁሉ የተለወጠው በመጀመሪያው የጳውሎስ የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞ ወቅት ነበር። ጳውሎስና በርናባስ በትንሹ እስያ ውስጥ ወንጌልን እየሰበኩ ሲዞሩ፥ ጥቂት አይሁዶችና ብዙ አሕዛብ በወንጌል ማመን ጀመሩ። በዚህ ጊዜ የአሕዛብ አማኞች ቁጥር ቀስ በቀስ የአይሁዶችን አማኞች ቁጥር እያጠፈ ይሄድ ጀመር። የአሕዛብ አማኞች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በአይሁዳውያን ክርስቲያኖች አእምሮ ውስጥ አንድ አስፈላጊ ጥያቄ ያቃጭል ጀመር። ይኸውም አሕዛብ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን የሚያገኙት እንዴት ነው? የሚለው ነበር። አብዛኞቹ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች አሕዛብ በክርስቶስ ከማመናቸው በተጨማሪ ወደ አይሁድነት መቀየር አለባቸው ብለው ያምኑ ነበር። ስለሆነም አንዳንድ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች አሕዛብ አማኞች መገረዝና የብሉይ ኪዳን ሕጎችን መጠበቅ እንዳለባቸው ያስተምሩ ጀመር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይጠቀስም፥ የቤተ መቅደስ፥ የምኩራብና የሌሎችም የአይሁዳውያን ባሕላዊ ልምምዶች ሁኔታ ከግርዘት ጋር አብሮ ሊነሣ የሚችል ጥያቄ ነበር። አሕዛብ ክርስቲያኖች ከተገረዙ፥ በቤተ መቅደስ ውስጥ ማምለክን ጨምሮ ሌሎች የአይሁዶች ባህሎችን ሁሉ መከተል ይኖርባቸው ነበር። ጴጥሮስና የቀድሞዎቹ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወያየት በተሰበሰቡ ጊዜ፥ አሕዛብ በክርስቶስ በማመናቸው ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እንደሚያገኙ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ወደ አይሁዳዊነት መለወጥና የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ልማዶች መቀጠል አያስፈልጋቸውም ነበር (የሐዋ. 15)። ይህም አሕዛብ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ ወደ አይሁድነት መለወጥ እንዳለባቸው ከሚያስተምረው የብሉይ ኪዳን አመለካከት የተለየ ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ ክፍፍል ተፈጠረ። እስከአሁን ድረስ፥ ሌሎች አይሁዶች ክርስትና ሌላው የይሁዲነት የሃይማኖት ክፍል እንደሆነ ያስቡ ነበር። ምንም እንኳን የአይሁድ መሪዎች ክርስቲያኖችን ቢያሳድዱም (የሐዋ. 9)፥ ተራ አይሁዳውያን የናዝሬቱ ኢየሱስን የሚከተሉትን አይሁዶች ወደ መቀበሉ ያዘነብሉ ነበር (የሐዋ. 2፡47)። ነገር ግን ከዚሁ የሐዋርያት ሥራ 15ቱ ውሳኔ በኋላ ክርስትና ከይሁዲነት የተለየ መሆኑ ጥርት ብሎ ታየ። ከዚህም የተነሣ፥ ለአይሁዳውያን ማኅበረሰብ ውጥረት እየጨመረ ይሄድ ጀመር። የማያምኑ አይሁዶች በሚያምኑት አይሁዶችና ክርስትና ላይ ይነሡ ጀመር። የማያምኑ አይሁዶች ክርስትና ከይሁዲነት የተለየ ሃይማኖት መሆኑን በመገንዘባቸው፥ ክርስቲያኖችን በግልጽ ይቃወሙ ጀመር። ይህ ተቃውሞ በተለይ አይሁዶችና አሕዛብ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያመልኩበት በትንሹ እስያ አይሎ ነበር። በኢየሩሳሌም፥ ሁሉም አማኞች በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያመልኩ በመሆናቸው፥ በመጀመሪያ አካባቢ ክርስቶስን በሚከተሉና በማይከተሉ ተራ አይሁዶች መካከል ግልጽ የሆነ ግጭት አልተከሰተም።

በኋላ በ60ዎቹ ዓ.ም አካባቢ ግን በፓለስታይን ሁኔታው ተለወጠ። ይሁዳ ከሮም ቅኝ ግዛት እንድትወጣ የዜጎቿ ፍላጎት እየጨመረ መጣ። የተለያዩ የዐማፅያን ቡድኖች ተመሠረቱ። በአሕዛብ ላይ ጠንካራ ተቃውሞ በይፋ ይሰነዝር ጀመር። ይህ ጥላቻ በሌሎችም አውራጃዎች ተሰራጨ።

ከፍተኛ የሀገር ወዳድነት ስሜት የሚሰማቸው አይሁዶች የመጡት ከፍልስጥኤም ነበር። በዚህ ጊዜ ክርስቲያን አይሁዶች አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። ክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸውን ትተው አይሁዳዊነታቸውን ያጠብቃሉ? አይሁዶች ለብቻቸው አሕዛብ ደግሞ ለብቻቸው የሚያመልኩባቸው ሁለት የተለያዩ ባዕዳዊ እምነቶች በመመሠረት አይሁዶችን ከአሕዛብ መለየት የቱ ይሻል ይሆን? በሮም ላይ የሚካሄደውን ዐመፅ ካልደገፉ፥ አገራቸውን እንደ ከዱ ከሃዲዎች ተደርገው ይቆጠሩ ጀመር። የማያምኑ አይሁዶች ክርስቲያን አይሁዶች ከአሕዛብ ተለይተው ወደ ጥንታዊ አምልኮአቸው እንዲመለሱ በመጠየቃቸው ምክንያት በይሁዳና በሮም ግዛቶች ሁሉ ትልቅ ውጥረት ተፈጠረ። ይህን አሳብ ለመቀበል ያልፈለጉ አይሁዶች አይሁዳዊነታቸውን እንደ ካዱ ተቆጠሩ። ከዚህም የተነሣ ከአይሁድ ወንድሞቻቸው ስደት ይሰነዘርባቸው ጀመር። በተለይ በ66 ዓ.ም በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁዶች በሮም ላይ በማመፃቸው ይኸው ውጥረት ከላቀ ደረጃ ላይ ደረሰ። በዚህ ጊዜ በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ አይሁዶች ዐመፁን የመደገፍ ወይም ከሮም ጋር የመተባበር ግዴታ ነበረባቸው። በ70 ዓ.ም ሮማውያን ከተማይቱን ቤተ መቅደሱን በመደምሰስ ዐመፁን እስከ ደመሰሱበት ጊዜ ድረስ ይኸው ዐመጽ አይሁዶችን ከፋፍሎአቸው ቆይቷል። የቤተ መቅደሱ መደምሰስ የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓት ከፍጻሜ አደረሰው።

15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በፖለቲካው (ጎሰኝነት፥ ብሔርተኝነት፥ ወዘተ...) ዓለም ውስጥ እየተከናወነ ያለው ነገር በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ግለጽ። ለ) ከመንፈሳዊ ቤተሰብህ ይልቅ ከጎሳህ ጋር መወገን ፈታኝ የሚሆነው እንዴት ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያን ወይም በሽማግሌዎች መካከል የሚፈጠረው ክፍፍል አንዳንድ ጊዜ ከጎሳዊ ውርስ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግለጽ። መ) ጎሰኝነት፥ ዘር ወይም ቤተሰባዊ ውርስ እንዲካሄዱ መፍቀድ ክርስቶስ ከጸለየበት (ዮሐ. 17 አንብብ) እና ጳውሎስ ካስተማረው (ገላ. 3፡28-29) እውነት ጋር የሚጻረረው እንዴት ነው?

ከኢየሩሳሌም መደምሰስ ቀደም ብሎ አማኝ አይሁዶች ወደ ይሁዲነት ሊመለሱ ውጥረት በበዛባቸው ወቅት፥ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ለክርስቲያን አይሁዶች ይህንን ጠቃሚ መልእክት ጽፎላቸዋል። ብዙ አይሁዶች ወደ ጥንታዊቷ እምነታቸው ለመመለስ እያሰቡ ነበር። «ጥንታዊ ልምምዶቻችን ለሙሴ፥ ለዳዊት፥ ለኢሳይያስና ለሌሎችም ጥሩዎች ከነበሩ፤ በክርስቶስ ማመናችንን ትተን ወደ እንስሳት መሥዋዕቶች ብንመለስ ምን አለበት?» ብለው ያስቡ ነበር። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ይህንን መልእክት ያስተላለፈው ወደ ጥንታዊ የአምልኮ መንገዳቸው ለመመለስ ያስቡ ለነበሩት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ነበር። ጀርባቸውን ለክርስቶስ ሰጥተው ወደ እንስሳት መሥዋዕቶች ቢመለሱ ምን ዓይነት አደጋዎች እንደሚጠብቃቸው ይነግራቸዋል። ክርስቶስ ለኃጢአታችው ስለ ሞተ፥ የእንስሳት መሥዋዕቶች ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሆነ እርሱን ለማምለክ ከእንግዲህ አማራጭ መንገዶች ሊሆኑ አይችሉም ነበር። ዛሬ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያድን ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ባቀረበው መሥዋዕት አማካኝነት ብቻ ነው። ደራሲው

በቅርቡ ቤተ መቅደሱ እንደሚደመሰስና የእንስሳት መሥዋዕቶች የሚቀርቡበት ሥርዓት እንደሚወገድ የሚያሳይ ትንቢታዊ መልእክት አስተላልፎአል (ዕብ. 18፡13)።

## የዕብራውያን መልእክት የተጻፈበት ዘመንና ቦታ

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፦ ዕብ. 13፡24 አንብብ። ደራሲው ሰላምታውን የሚልከው ከየት ሆኖ ነው? |

የዕብራውያን መጽሐፍ፥ «ከኢጣልያ የሆኑቱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል» በማለት መልእክቱን ይደመድማል። ይህ ዐረፍተ ነገር ሁለት ትርጉሞች ሊሰጥ ይችላል። በመጀመሪያ፥ ደራሲው በኢጣልያ አገር እንደሚኖርና እዚያው ከነበሩት ክርስቲያኖች በሌላ ስፍራ ላሉት አንባቢዎች ሰላምታ እንደሚያቀርብ ሊያመለክት ይችላል። ሁለተኛ፥ ደራሲው በየትም ስፍራ ቢሆን፥ አንዳንድ የኢጣልያ አማኞች (እንደ ጵርስቅላና አቂላ) ከእርሱ ጋር እንደነበሩ ሊያሳይ ይችላል። እነዚህ የኢጣልያ አማኞች በሮም ለሚኖሩ አንባቢዎች ሰላምታ ልከውላቸው ይሆናል። ምንም እንኳን የተለያዩ ምሁራን ይህን መልእክት ከሮም፥ ከኢየሩሳሌም፥ ከአሌክሳንደሪያ፥ ወይም ከሌሎች ከተሞች እንደ ተጻፈ የሚያመለክቱ የተለያዩ ንድፈ አሳቦችን ቢያቀርቡም፥ ደራሲው የዕብራውያንን መልእክት በጻፈበት ወቅት የት እንደነበረ በትክክል መናገር አይቻልም።

በጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ጽሑፎች ውስጥ የዕብራውያን መልእክት በቀዳሚነት የተጠቀሰው በ95 ዓ.ም ሲሆን፥ ይህንንም ያደረገው የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። ይህም መጽሐፉ በዚያን ጊዜ እንደ ተጻፈ ያመለክታል። ጢሞቴዎስ ገና አልሞተም ነበር (ዕብ. 13፡23)። ለአይሁዶች ወንጌልን የመሰከሩና ክርስቶስን በዓይነ ሥጋቸው የተመለከቱ አንዳንድ አገልጋዮች እንዲሁ በሕይወት ነበሩ (ዕብ. 2፡3)። ደራሲው የቤተ መቅደሱን መደምሰስ አለመግለጹ፥ አይሁዶች የእንስሳት መሥዋዕቶች ያቀረቡ መሆናቸው (ዕብ. 10፡2)፥ እንዲሁም ካህናት ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገለገሉ መሆናቸው (ዕብ. 5፡1-3፥ 7፡23፥ 27፤ 8፡3-5፤ 9፡6-9)፥ ይህ መልእክት ቤተ መቅደሱ ከተደመሰሰበት እና የእንስሳት መሥዋዕት ከቆመበት ከ70 ዓ.ም በፊት እንደ ተጻፈ ያመለክታል። የዕብራውያን መልእክት የተጻፈበት ትክክለኛው ጊዜ ከ60-68 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ይመስላል።

## የዕብራውያን መልእክት ዓላማ

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፦ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ። ዕብ. 1፡1-4፤ 3፡3፤ 6፡9፤ 7፡7፤ 19፥22፤ 8፡6፤ 9፡23፤ 10፡34፤ 11፡16፥35፥ 40፤ 12፡24። የዕብራውያን መልእክት ክርስቶስ ከምን ከምን እንደሚበልጥ ይናገራል? |

የመጀመሪያ ዓላማ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዶች በብሉይ ኪዳን ዘመን ታላቅ ነው ብለው ከሚያስቡት ነገር ሁሉ እንደሚበልጥ ለማሳየት። አይሁዶች ረዥም ዘመናት ውርሳቸውና በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር በነበራቸው ልዩ ቃል ኪዳን ምክንያት ከፍተኛ የትምክህተኝነት ስሜት ይሰማቸው ነበር። የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያረፈበት ቃልና ኪዳናት ነበሩዋቸው። አይሁዶች

በመላእክት የተሰጠና፥ ከሙሴ ሕግን የተቀበሉና እግዚአብሔር ባዘዛቸው መንገድ አምልኮአቸውን የሚያካሂዱ፥ ወዘተ... በመሆናቸው ይኩራሩ ነበር። አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በተለይ ከወገኖቻቸው ስደት በተነሣ ጊዜ በእነዚህ ነገሮች ላይ አጽንኦት ወደ መስጠቱ አቅጣጫ ለመመለስ እየተፈተኑ ነበር። ደራሲው ለዚህ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት አይሁዶች ወደ ብሉይ ኪዳን የአምልኮ መንገድ ቢመለሱ፥ በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ማመናቸውን እንደ ካዱ ያስረዳል። ክርስቶስ ታላቅ ሰው ነው ብሎ ቢያስብም እንኳን፥ ወደ ብሉይ ኪዳን መመለሱ የክህደት ተግባር ነበር። ለኃጢአታቸው መሞቱን ጭራሽ እንዳልተፈጸመ ታሪክ ከንቱ ማድረጋቸው ነበር። የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ ባለመቀበላቸው ሌላ የመዳን መንገድ አያገኙም ነበር። እግዚአብሔር የእንስሳት መሥዋዕቶችን የደኅንነትና የይቅርታ መንገድ አድርጎ የሚቀበልበት ጊዜ አልፎ ነበር።

ደራሲው የክርስቶስን ታላቅነትና እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ያቀደው ነገር ሁሉ ፍጻሜው መሆኑን ያስረዳል። ብሉይ ኪዳን እንደ ጥላ ሲሆን፥ እውነታው ክርስቶስ ነበር። ክርስቶስ የሚገልጣቸውን ነገሮች በተምሳሌትነት አሳይቷል። ደራሲው ለምን አይሁዳውያን ክርስቶስ ላይ ዓይኖቻቸውን መትከል እንዳለባቸውን ወደ ይሁዲነት መመለስ እንደሌለባቸው ሲገልጽ፥ የሚከተሉትን ነጥቦች አብራርቷል። ክርስቶስ ከሚከተሉት ሁሉ እንደሚበልጥ፥ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ እንመለከታለን፡-

ሀ) ክርስቶስ እግዚአብሔር ከገለጣቸው ቀደምት መገለጦች፥ እንደ ኢሳይያስ ካሉት ነቢያትም የሚበልጥ ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ቃሉን የሰጠው በደካማ የሰው ልጆች በኩል ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን አምላክ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነበር። እርሱም በአካል ተገኝቶ በሰዎች መካከል ያደረና እግዚአብሔርን በታላቅ አኳኋን የገለጸ አምላክ ነው (ዕብ. 1፡1-4)።

ለ) ክርስቶስ አይሁዶች፥ ከሚያከብሩአቸው የብሉይ ኪዳን መላእክት በላይ ነበር። ደራሲው መላእክት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲያገለግሉ የሚልካቸው መናፍስት መሆናቸውን ይናገራል። መላእክት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩ። ክርስቶስ ግን አምላክና ሰዎች እንዲሁም መላእክት የሚሰግዱለት መሆኑን ተመልክቷል (ዕብ. 1፡3-2፡18)።

ሐ) ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ታላቅ ሕግ ሰጪ ከነበረው ከሙሴ በላይ ነው (ዕብ. 3፡1-6)። ሙሴ ምንም ያህል ታላቅ ቢሆንም፥ የቤቱ አካል ወይም የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል ነበር። ክርስቶስ ግን አምላክ እንደ መሆኑ፥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ በላይ ነበር። እርሱ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቤት ንድፍ እንደሚያወጣና እንደሚቆጣጠር ዕቅድ ነዳፊ ነበር።

መ) ክርስቶስ ከሊቀ ካህናቱ ከአሮን ይበልጣል (ዕብ. 5፡1-10)። አሮንና ከእርሱ በኋላ የነበሩት ሊቀ ካህናት በሙሉ ኃጢአተኞች በመሆናቸው፥ ለራሳቸው ኃጢአቶች መሥዋዕቶችን ማቅረብ ያስፈልጋቸው ነበር። አሮን ሰው በመሆኑ በሞት እንደ ተሸነፈና ሌሎች (ብዙዎች መንፈሳዊያን ያልሆኑ የሊቀ ካህናትነት አገልግሎቱን እንደተቀበሉ

ተገልጾአል። ክርስቶስ በብዙ መንገድ ከአሮን ይበልጣል። ክርስቶስ ካህንም ንጉሥም በመሆኑ ከአሮን ይበልጣል። ኃጢአት የሌለበት እና ፍጹም በመሆኑ ከአሮን ይበልጣል። ሰውም አምላክም በመሆኑና ከዚህም የተነሣ ሰውንና እግዚአብሔርን ለመወከል በመቻሉ ከአሮን ይበልጣል። አሮን አገልግሎቱ ባለመጠናቀቁ ምክንያት ለማረፍ ያልተፈቀደለት ሲሆን፥ ክርስቶስ የመሥዋዕትነት አገልግሎቱን ስላጠናቀቀና እንደገና መድገም ስለማያስፈልገው በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል። በአሮንና በሌቀ ካህናት ዘመን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርቡ የሚከላከል መጋረጃ በቤተ መቅደስ ውስጥ ነበር። ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ግን መጋረጃው ከላይ እስከ ታች ተቀደደ፤ በመሆኑም አማኞች በድፍረት ወደ ጸጋው ዙፋን ሊቀርቡ ይችላሉ)።

ሠ) ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች የበለጠ መሥዋዕት ነው (ዕብ. 9፡11-14)። እንስሳት ጊዜያዊ የኃጢአት ይቅርታ ከማስገኘት ያለፈ ፋይዳ የላቸውም። እንስሳት እንደ መሆናቸው፥ ለሰዎች ኃጢአቶች ምትክ ሆነው ሊሞቱ አይችሉም። ክርስቶስ ግን ሰውም አምላክም በመሆኑ፥ የበለጠ ታላቅ መሥዋዕት ሆኗል። የብሉይ ኪዳን እንስሳት ባለማቋረጥ መሠዋት የነበረባቸው ሲሆን (በቀን ብዙ እንስሳት፥ በዓመት በሚሊዮን የሚቆጠር)፥ የክርስቶስ አንድ መሥዋዕት ከአዳም ጀምሮ እስከ መጨረሻው ግለሰብ ያሉትን ሰዎች ኃጢአት ለማንጻት ችሏል። የእንስሳት መሥዋዕቶች ከፊልና ጊዜያዊ የኃጢአት መሸፈኛ ነበሩ። የክርስቶስ መሥዋዕት ግን ዘለቄታዊ በመሆኑ፥ በእርሱ የሚያምኑትን ለዘላለም ያነጻቸዋል።

ረ) ክርስቶስ በላቀ ድንኳን ወይም ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገለግላል (ዕብ. 9፡1-10)። ሰብአዊ ካህናት የሰማያዊቱ ቤተ መቅደስ ነጸብራቅ በሆነ እና ፍጹምነት በጎደለው የመገናኛ ድንኳን ወይም ቤተ መቅደስ ውስጥ አገልግለዋል። (ይህ ልጆች የሚሰሩት የቆርቆሮ መኪና ከእውነተኛ ትልቅ መኪና እንደሚያንስ ማለት ነው።) ክርስቶስ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሆነችው መንግሥተ ሰማያት ውስጥ ያገለግላል። ምንም እንኳን ክርስቶስ በምድር ላይ ቢሞትም፥ እግዚአብሔር በሚቀበለው መንገድ ኃጢአት ይቅርታ የሚያገኝበትን መንገድ ለማቅረብ ደሙን (ሕይወቱን የሠዋው) በሰማይ ነበር።

ክርስቶስ የብሉይ ኪዳንና የአይሁዶች የአምልኮ ሥርዓት ማዕከላት ከሆኑት ነገሮች ሁሉ ስለሚበልጥ፥ ከክርስቶስ ርቆ ፍጹም ወዳልሆነ፥ ወዳልተሟላና በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ሊጣራ ወደ ተቃረበ የአምልኮ ሥርዓት መመለሱ ሞኝነት ነበር።

18ኛ ጥያቄ፦ ሀ) እንደ ክርስቶስ ታላቅ ሳይሆኑ ዛሬ ክርስቲያኖችን የሚማርኩ የሚመስሉትን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር። ለ) ክርስቲያኖች በእነዚህ ነገሮች በማመን እግዚአብሔር በሕይወታቸው እንዲታዩ የሚፈልጋቸውንና ዘላለማዊ በረከት የሚያመጡትን ነገሮች የሚያጥፉትን ነገሮች ግለጽ። በሕይወትህ ውስጥ የሚማርኩ፥ ዳሩ ግን በዘላለም ዘመን እንጻር ሲታዩ መልካም ያልሆኑና እምነትን ሊያወድሙ የሚችሉ ነገሮች መኖራቸውን ለማወቅ ሕይወትህን መርምር። እነዚህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ተናዘዝና ከጊዜያዊ ነገሮች ይልቅ ወሳኝ የሆኑትን ለመከተል ቁረጥ።

19ኛ ጥያቄ፡- ዕብ. 2፡1-4፤ 3፡12-14፤ 4፡1-2፤ 5፡11-6፡8፤ 10፡26-31 አንብብ። በእነዚህ ምንባቦች ውስጥ ለክርስቲያኖች የተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ምን ምን ናቸው?

ሁለተኛ ዓላማ፡ አማኞች ከስደት ለማምለጥ ብለው በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት እንዳይክዱ በጽኑ ለማስጠንቀቅ። ክርስቲያኖች እምነታቸውን እንዳይክዱ የሚያሳስቡ እጅግ ጠንካራ ማስጠንቀቂያዎች በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ይገኛሉ። አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ከአይሁዳውያን ወገኖቻቸው የሚመጣውን ስደት ፈርተው ነበር። ብዙዎቹ እምነታቸውን ለመደበቅ፥ ወይም እምነታቸውን ክደው ወደ ይሁዲነት ለመመለስ እያሰቡ ነበር።

የዕብራውያን መልእክት ደራሲ እምነታቸውን ከመካድ ይልቅ በድፍረት ስደትን እንዲቀበሉ ይመክራቸዋል። የአይሁድ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ብዙ ካወቁ በኋላ እምነታቸውን ቢክዱ፥ ዘላለማዊ ቅጣቶች ይከተሏቸዋል። ሌላ የመዳን መንገድ አያገኙም። ስለሆነም ወደ ኋላ ከመመለስ ይልቅ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደ ነበሩትና ከጊዜያዊ ችግሮች አሻግረው የሰማይን በረከቶች እንደ ተመለከቱት የእምነት ጀግኖች መሆን ያስፈልጋቸው ነበር። ሊቀ ካህናችን የሆነው ክርስቶስ ደግሞ ትግላችንን ስለሚያውቅ እነዚህን ፈተናዎች እንድናሸንፍ ይረዳናል

20ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢትዮጵያ ብዙ አማኞች እምነታቸውን የካዱት ለምንድን ነው? ለ) እንደ እነዚህ ዓይነት ውሳኔዎች ስለሚያስከትሏቸው ዘላለማዊ ውጤቶች የዘነጉት ነገር ምንድን ነው? ሐ) ሰዎች እምነታቸውን መካድን እንደ አማራጭ እንዳይወስዱ ቤተ ክርስቲያን እንዴት በተሻለ ሁኔታ ልታስተምራቸው ትችላለች?

## የዕብራውያን መልእክት ልዩ ባሕርያት

1. የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ እንደ ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ክርስቶስ ኢየሱስ ወይም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እያለ አይጽፍም። ነገር ግን አንዱን ስም ብቻ (ኢየሱስ ወይም ክርስቶስ) ሲል ይጽፋል።

2. ከመጨረሻዎቹ ጥቂት ቁጥሮች በስተቀር፥ የዕብራውያን መልእክት ደብዳቤ አይመስልም። ደራሲው ስሙን በማስተዋወቅ ሰላምታ የሚሰጥበት መግቢያ በመጽሐፉ ውስጥ አይገኝም። ይህ እምነታቸውን ለመካድ ለሚያስቡ የተወሰኑ የአይሁድ ክርስቲያኖች የተላከ ሰነድ ወይም ስብከት ነው።

3. በመጽሐፉ ውስጥ አምስት «የማስጠንቀቂያ» ምንባቦች አሉ (ዕብ. 2፡1-4፤ 3፡7-4፡13፤ 5፡11-6፡8፤ 10፡19-39፤ 12፡14-29)። (ማስታወሻ፡ አንዳንድ ምሁራን ሰባት የማስጠንቀቂያ ምንባቦች እንዳሉ ይናገራሉ። እነዚህም፥ ዕብ. 2፡1-4፤ 3፡7-19፤ 4፡11-13፤ 5፡11-6፡20፤ 10፡26-31፤ 12፡25-29፥ 13፡15-19)። እነዚህ ምንባቦች አማኞች ክርስቶስን ክደው ወደ ቀድሞው አኗኗራቸው እንዳይመለሱ ጽኑ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣሉ። ደኅንነትና ዘላለማዊ በረከቶች የሚገኙት በክርስቶስ ብቻ ነው።

4. የዕብራውያን መልእክት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በሚገባ የሚያውቁትን ብሉይ ኪዳን በብዙ ስፍራዎች ላይ ይጠቅሳል። ነገር ግን ደራሲው የተጠቀመባቸው የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የተወሰዱት ከአረማይክ

ወይም ዕብራውያን የብሉይ ኪዳን ሳይሆን፥ ሴብቱዋጄንት ከሚባለው የግሪክ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ነው። ይህን እነዚህ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች የዕብራውያን የብሉይ ኪዳን በብዛት ከግልጋሎት ላይ ከሚውልበት ኢየሩሳሌም ከተማ ሳይሆን፥ የግሪክ የብሉይ ኪዳን አገልግሎት በሚሰጥባት በሌላ የሮም ግዛት ውስጥ እንደነበሩ ያመለክታል። ደራሲው ከብሉይ ኪዳን ሲጠቅስ፥ በአብዛኛው ከሙሴ መጻሕፍት ወይም ከመዝሙራት ይጠቅሳል። እንደ ብዙዎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሙሴ ወይም ዳዊት ምንባቡን እንደ ጻፈው ከመናገር ይልቅ እግዚአብሔር (ዕብ. 2፡6)፥ ኢየሱስ (ዕብ. 2፡11-12) ወይም መንፈስ ቅዱስ (ዕብ. 3፡7) ምንባቡን እንደተናገረ ይገልጻል። በዚህም የብሉይ ኪዳንን መለኮታዊ ሥልጣን ከፍ አድርጎ ያሳያል።

5. ደራሲው እንደ «የሚሻል» (ዕብ. 1፡4፤ 6፡9፤ 7፡7፥ 22፤ 8፡6፤ ወዘተ...)፤ ለ) «ዘላለማዊ» (ዕብ. 1፡8፤ 5፡6፥ 9፤ 6፡1-2፥ 20፤ 7፡11፥ 17፥ 21፥ 24፥ 28፤ ወዘተ...)፤ ሐ) «ፍጹም» (ዕብ. 2፡10፤ 5፡9፤ 7፡11፥ 19፤ 9፡9፤ 10፡1፥ 14፤ ወዘተ...) መ) «ሰማያዊ» (ዕብ. 1፡10፤ 3፡1፤ 4፡14፤ 6፡4፤ ወዘተ...) ባሉት ቃላት ላይ ትኩረት ይሰጣል።

6. ደራሲው ትምህርቱ ራሱንም እንደሚያጠቃልል የሚያመለክቱትን አገላለጾች ይጠቀማል (ዕብ. 4፡1፥ 11፥ 14፥ 16፤ 6፡1፤ 10፡22-25፤ 12፡1-3፥ 28፤ 13፡1፥5፥ 13፥15።)

የዕብራውያን መልእክት ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ሰፊ ማብራሪያ ያቀርባል። ክርስቶስ ካህናችን መሆኑን፥ ለኃጢአታችን መሠዋቱን፥ እንዲሁም ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን ያብራራል።

## የዕብራውያን መዋቅር

1. ዕብራውያን በጥንቃቄ የተዋቀረ መጽሐፍ ነው። ደራሲው ክርስቶስ ከሌሎች የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ማዕከላት እንደሚበልጥና የእነዚሁ የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓቶች ፍጻሜ የሆነላቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር መልእክቱን ግሩም አድርጎ አዋቅሮአል። በመሠረታዊነት ይህ መልእክት ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት።

ሀ. ዕብ. 1፡1-10፡18 የመጽሐፉን መሠረታዊ ትምህርት ያቀርባል። ይኸውም አይሁዶች ጥንታዊ ሃይማኖታቸውን ታላቅ እንዳደረጉ ከሚያስቧቸው ነገሮች ሁሉ ክርስቶስ እንደሚበልጥ የሚያሳይ ነው። ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን መጻሕፍት፥ መላእክት፥ ሙሴ፥ ኢያሱ፥ አሮን፥ የእንስሳት መሥዋዕቶች፥ ወዘተ... እንደሚበልጥ ተገልጾአል።

ለ) ዕብ. 10፡19-13፡25 በእምነት መኖር ምን ማለት እንደሆነና አማኞች እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ በመጣል እንዴት በታማኝነት እንደሚጸኑ ያብራራል። ወደ መንግሥተ ሰማይ እስክንደርስ ድረስ ለእርስ በርሳችን ታማኞች ሆነን መጽናት ይኖርብናል። መንግሥተ ሰማይ አማኞችን ሁሉ በመጠባበቅ ላይ ያለች እውነተኛይቱ ኢየሩሳሌም ናት።

2. ደራሲው ትምህርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ በአመዛኙ ቀም ይልና የሚያስተምራቸው እውነቶች ምን ዓይነት አስከትሎት እንዳላቸው ለአንባብያኑ ያስገነዝባል። በተለይም እንዲህ ዓይነቱን ማስጠንቀቂያ

የሚሰጠው ክርስቶስን ክዶ ወደ ይሁዲነት መመለስ አደገኛ መሆኑን ለማመልከት ነው። እነዚህ አምስት (አንዳንድ ምሁራን እስከ ሰባት ያደርጓቸዋል) የማስጠንቀቂያ ምዕራፎች (ዕብ. 2፡1-4፤ 3፡7-4፡13፤ 5፡11-6፡8፤ 10፡19-39፤ 12፡14-29) ቅንፋዊ ምንባቦች በመባል ይታወቃሉ፥ ለዚህም ምክንያቱ እነዚህ ምንባቦች ወደኋላ ለመመለስ የሚያስቡትን ሰዎች ለማስጠንቀቅ ሲሉ የክርክሩን ይዘት የሚያቋርጡ መሆናቸው ነው። ደራሲው ማስጠንቀቂያውን ከሰጠ በኋላ፥ ወደ አሳቡ በመመለስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንደሚበልጥ የሚያምንባቸውን ማረጋገጫዎች ያቀርባሉ።

## የዕብራውያን አስተዋጽኦ

1. ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ከተከበሩት ነገሮች ሁሉ በላይ ነው (ዕብ. 1፡1-10፡18)።

   ሀ. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ከፍተኛው መገለጥ ነው (ዕብ. 1፡1-3)።

   ለ) ክርስቶስ ከመላእክት ይበልጣል (ዕብ. 1፡4-2፡18)።

   (የመጀመሪያው የማስጠንቀቂያ ምንባብ- ዕብ. 2፡1-4)

   ሐ) ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል (ዕብ. 3፡1-19)።

   መ) ሁለተኛው የማስጠንቀቂያ ምንባብ- ዕብ. 3፡7-4፡13። [(ክርስቶስ ከኢያሱ እንደሚበልጥ የሚናገረውን ክፍል ያጠቃልላል። (ዕብ. 4፡1-13)]

   ሠ. ክርስቶስ ከአሮን ወገን ከሆኑት ሊቀ ካህናት ይበልጣል (ዕብ. 4፡14-7፡28)።

   1. ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ለመሆን ብቁ ነው (ዕብ. 4፡14-5፡10)።
   2. ሦስተኛ የማስጠንቀቂያ መልእክት (ዕብ. 5፡11-6፡20)።
   3. የክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ከአሮን ይበልጣል (ዕብ. 7)።

   ረ) የክርስቶስ አገልግሎትና መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን ዘመን ከነበሩት ይበልጣል (ዕብ. 8-10)።

   1. የክርስቶስ አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን በሚበልጠው አዲስ ኪዳን ላይ የተመሠረተ ነው (ዕብ. 8)።
   2. የክርስቶስ አገልግሎት ከመገናኛ ድንኳን በሚበልጠው ሰማያዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ ይካሄዳል (ዕብ. 9፡1-12)።
   3. የክርስቶስ መሥዋዕት ከእንስሳት መሥዋዕቶች ይበልጣል (ዕብ. 9፡13-10፡18)።

2. ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ነገሮች ሁሉ ስለሚበልጥ፥ እርሱን እንዴት መከተል እንዳለብን (ዕብ. 10፡19-13፡25)

   ሀ. አራተኛው የማስጠንቀቂያ ምንባብ (ዕብ. 10፡19-39)።

   ለ. ክርስቶስን መከተል እምነትን ይጠይቃል (ዕብ. 11)።

ሐ. ክርስቶስን መከተል ማለት በመንፈሳዊ ሩጫችን መጽናት ማለት ነው (ዕብ. 12፡1-13)።

መ. አምስተኛው የማስጠንቀቂያ ምዕራፍ (ዕብ. 12፡14-29)።

ሠ. እንደ የክርስቶስ ተከታዮች እንዴት መመላለስ እንዳለብን (ዕብ. 13፡1-17)።

ረ. መደምደሚያ (ዕብ. 13፡18-25)

## ሦስተኛ ቀን ዕብራውያን 1፡1-4፡13

ታረቀች ያደገችው በጠንካራ የኦርቶዶክስ አማኞች ቤተሰብ ውስጥ ነበር። ከትንሽነቷ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በጥንቃቄ መከተል እንዳለባት ተምራለች። በአብዛኛው ተአምረ ማርያም ወይም የኦርቶዶክስን እምነት የሚያጠናክሩትን ሌሎች መጻሕፍት እንድታነብ ትመከር ነበር። ታረቀች በተጨማሪም፥ ክርስቶስ በቀዳሚነት አምላክ እንጂ ሰው እንዳልሆነ፥ እርሱ ታላቅ አምላክ በመሆኑ ምክንያት ሰዎች በቀጥታ ወደ እርሱ ሊደርሱ እንደማይችሉ ተምራለች። በመላእክት ወይም የክርስቶስ እናት በሆነችው ድንግል ማርያም በኩል ልትጸልይ እንደምትችል ተነግሯታል። በማርያም በኩል ከጸለየች እርሷ ጥያቄዋን ለክርስቶስ እንደምታቀርብላት ተረድታለች። ምክንያቱም ጥሩ ልጆች ሁሉ እናቶቻቸውን ይታዘዛሉ። ታረቀች እግዚአብሔር ከእርሷ የሚፈልገው በተወሰኑ ቀናት እንድትጾምና በበዓል ቀናት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄደች መላእክትን እንድታገኝ፥ ቅዱሳንንና ድንግል ማርያምን እንድታከብር መሆኑን አመነች። በመሆኑም እነዚህን ልምምዶች ጠንቀቅ ታደርግ ጀመር።

አንድ ቀን ታረቀች የኦርቶዶክስ የተሐድሶ ቡድን አባል ከሆነች አማኝ ጋር ተገናኘች። በዚህም ጊዜ ታረቀች የተሐድሶ ቡድን አባል የሆነችው አማኝ ለየት ያለ የንግግር፥ የጸሎትና የአምልኮ ዘይቤ እንደምትከተል ተገነዘበች። ልዩነቱ ከምን እንደ መጣ ስትጠይቅ፥ ይህች የተሐድሶ አባል የክርስትና እምነት አስኳሉ ክርስቶስ እንደሆነ ገለጸችላት። ማምለክ፥ መጸለይ፥ መዘመርና ማክበር ያለብን ክርስቶስን ነው ስትል ገለጸችላት። ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ከመሆኑ በተጨማሪም ፍጹም ሰውና ሊቀ ካህናችን በመሆኑ ሩቅና የማይደረስበት ሳይሆን፥ በቀጥታ ልንጸልይለት የምንችለው አምላክ ነው አለቻት። ደኅንነት በኦርቶዶክስ ቤተሰብ ውስጥ በመወለድ፥ ለድሆች በመመጽወት፥ ለቅድስት ማርያም ወይም ለመላእክት በመጸለይ፥ ሃይማኖታዊ በዓላት ላይ በመገኘት፥ ወዘተ... እንደማይገኝ አብራራችላት። ደኅንነት ክርስቶስ ለኃጢአቷ መሥዋዕት ሆኖ እንደ ሞተ በማመን የምታገኘው የግላዊ ውሳኔ ውጤት እንደሆነም ገለጸችላት። ይህም ክርስቶስን የመከተልና ከእርሱ ጋር ኅብረት የማድረግን ፍላጎት እንደሚያሳድር አስረዳቻት።

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ የኦርቶዶክስ አማኞች ከክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት ለመመሥረት የሚቸገሩት ለምንድን ነው? ከክርስቶስ ይልቅ ከቅዱሳን፥ አማልእክት፥ ከድንግል ማርያም ጋር መዛመድ የሚቀላቸው ለምንድን ነው? ሐ) ከቅዱሳን፥

ከመላእክት፥ ወይም ከድንግል ማርያም ይልቅ በክርስቶስ ላይ ማተኮር ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ።

የዕብራውያን መልእክት እንደ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በመልካም ነገሮች ላይ ዓይኖቻቸውን ላሳረፉ አይሁዶች የተጻፈ መልእክት ነው። እነዚህ መልካም ነገሮች ግን እጅግ አስፈላጊዎች አልነበሩም። የአይሁድ አማኞች የብሉይ ኪዳን ጽሑፎችን፥ የእንስሳት መሥዋዕቶችን፥ ካህናቶቻቸውን ወይም እንደ ሙሴ ያሉትን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ማክበርን፥ እንዲሁም የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ወሳኝ አድርገው ይቆጥሩ ነበር። እነዚህ መልካም ነገሮች ላይ በማተኮር፥ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በቀጥታ ለመገናኘት የሚፈልግ መሆኑን ዘነጉ። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሥጋ ለብሶ ሲመጣ አይሁዶች የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃሎች ፍጻሜ አድርገው ሊቀበሉት አልፈለጉም። እግዚአብሔር አዲስ ነገር እንዳደረገ ሳያውቁ ባህላዊ እምነቶቻቸውንና ልምምዶቻቸውን መከተላቸውን ቀጠሉ።

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተመሳሳይ ዝንባሌ ይታያል። መልካም አስተሳሰብ ያላቸው ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎቻቸው በካህናቶቻቸው፥ በታቦት፥ በሃይማኖታዊ ባርነት ወይም በጾም ላይ ያተኩራሉ። ቅዱሳንን፥ መላእክትንና ድንግል ማርያምን በጥንቃቄ ያከብራሉ። ይህን በማድረጋቸው ግን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደ ልጆቹ በቀጥታ ከእርሱ ጋር እንዲገናኙ የሚፈልግ መሆኑን ለማየት ታውረዋል። ክርስቶስ በሞተበት ጊዜ ሰውንና እግዚአብሔርን ይለይ የነበረው የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተቀዷል። አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ የግል ኃጢአታቸው መሥዋዕት እንደሆነ የሚያምኑ ሰዎች በሙሉ በድፍረትና በልበ ሙሉነት እግዚአብሔር ወደሚገኝበት የጸጋው ዙፋን ሊቀርቡ ይችላሉ። በዚህም ጊዜ ከሚወዳቸውና ከሚንከባከባቸው ሰማያዊ አባታቸው ጋር እንደሚነጋገሩ ይረዳሉ።

የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ታላቅ መጽሐፍ የጻፈው እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ያከናወነውን ተግባር ቸል እያሉ በትውፊቶችና ውጫዊ ነገሮች ላይ ማተኮሩ ስሕተት መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህ መጽሐፍ ከውጫዊ ነገሮች ወይም ከትውፊቶቻችን በላይ የእምነታችን ጀማሪና ራስ በሆነው (ዕብ. 12፡2-3) በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ዓይናችንን እንድንተክል ያሳስበናል። ይህ መልእክት አይሁዶች በብሉይ ኪዳን አምልኮ ውስጥ እጅግ ከሚያከብሯቸው ነገሮች ሁሉ ክርስቶስ እንደሚበልጥ በጥንቃቄ ያሳያል። ደራሲው አይሁዶች ወደ ታሪካዊና ትውፊታዊ አምልኳቸው በመመለስ ክርስቶስ እንዳልሞተላቸው ሁሉ የቀድሞ አኗኗራቸውን እንዳይቀጥሉ በጽኑ ያስጠነቅቃቸዋል። ዛሬ እኛ እንደ ካህናትና ዝነኛ ሰባኪዎች በመሳሰሉት ሰዎች ትኩረት እንዳናደርግ ያስጠነቅቀናል። እንደ ማርያም ወይም መላእክት ያሉትን አማላጆችን መጠቀም የለብንም። እንዲህ የምናደርግ ከሆነ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረጉ በቂ እንዳልሆነ መግለጻችን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለመለካት የቤተ ክርስቲያን አባልነት፥ ለደሃ መመጽወት፥ የአንድ ቤተ እምነት አባል መሆን፥ በልሳን መናገር ወይም ፈውሶች በመሳሰሉት

ውጫዊ ነገሮች ላይ ማተኮር የለብንም። ይልቁንም መንፈሳዊ ዓይኖቻችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሊያርፉና ከእርሱ ጋር ያለማቋረጥ ግንኙነት ልንፈጥር ይገባል።

> 22ኛ ጥያቄ፡- ዕብ. 1፡1-4፡13 አንብብ። ሀ) ደራሲው ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደሚበልጥ የሚያሳየው እንዴት ነው? ለ) ደራሲው ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ የሚያሳየው እንዴት ነው? ሐ) ደራሲው ክርስቶስ ከሙሴ እንደሚበልጥ የሚያሳየው እንዴት ነው? መ) ደራሲው ለኢያሱ የተገባለትን ዕረፍት የሚያወርሰው ክርስቶስ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው? ሠ) በተሳሳቱ ነገሮች ለሚታመኑ ወይም በክርስቶስ ላይ የነበራቸውን እምነት ለሚክዱ ሰዎች የተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ምን ምንድን ናቸው?

## ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ከተከበሩት ነገሮች ሁሉ በላይ ነው

(ዕብ. 1፡1-10፡18)

1. ክርስቶስ የሚበልጥ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው (ዕብ. 1፡1-3)።

ልክ እንደኛው አይሁዶችም የሃይማኖታቸው ሁሉ መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (ብሉይ ኪዳን) መሆናቸውን ያምኑ ነበር። እግዚአብሔር ለግለሰቦች እራሱን ለመግለጡ እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የእግዚአብሔርን ቃላት ለመጻፍ በቅተዋል። አይሁዶች ቅዱሳት መጻሕፍትንና እግዚአብሔር መልእክቱን ለመጻፍ የተጠቀመባቸውን አገልጋዮች እጅግ ያከብሩአቸዋል። አይሁዶች ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የገለጠው በእስትንፋስ እግዚአብሔር የተጻፈ መልእክት እንደሆነና ይህም በቀዳሚነት ክርስቶስን ለሰዎች የሚገልጥ እንደሆነ ያምኑ ነበር። የሚገርመው ግን አይሁዶች አካላዊውን መጽሐፍ እጅግ እያከበሩት (የእግዚአብሔርን ቃል ለማክበር ብራናውን ይስሙት ነበር።)፤ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እጅንአት የሰጡበትን ክርስቶስን ለማወቅ አልቻሉም። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የእግዚአብሔር የመጨረሻው መገለጥ የሆነው ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከታዩት መገለጦች ሁሉ እንደሚበልጥ ለመግለጽ ማብራሪያውን ይጀምራል።

ደራሲው ታሪክን በሁለት ይከፍላል። እነዚህም *ከጥንት ጀምሮ* እና *በዚህ ዘመን መጨረሻ* የሚሉ ናቸው። ጥንት ወይም በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ እግዚአብሔር ራሱን ገልጦ ለአይሁዶች ተናግሯል። እግዚአብሔር ራሱን ለነቢያት ለመግለጥ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሟል። አንዳንዶች ራእዮችን አይተዋል። ሌሎች ደግሞ ሕልም አልመዋል። ሌሎች ቃሉን በሚጽፉበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ላይ ሲንቀሳቀስ ይሰማቸው ነበር። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ድምጽ ከመስማታቸው የተነሣ የጻፉ ነቢያትም ነበሩ። መልእክቱ የመጣበት መንገድ ወሳኝ አልነበረም። ዋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱ እና የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ ብቻ ነበር።

ክርስቶስ በመጣ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ከብሉይ ኪዳን እጅግ በጠራ መንገድ ገልጧል። በሌላ ሰው በኩል ከመናገር ይልቅ ራሱ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ምድር መጣ። በዚህ ጊዜ በመናገር ብቻ ሳይሆን፥ ለሰዎች በሚታይ መልኩ የእግዚአብሔርን ባህሪ እና

ፈቃድ በግልጽ አሳይቷል። ደራሲው ክርስቶስ መልካም ሰው፥ ወይም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩትን ነቢያት የሚመስል ሰው ብቻ እንዳልሆነ ይናገራል። ይልቁንም እርሱ ራሱ አምላክ ነበር። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያስተላለፈው መገለጥ ከሌሎች የሚበልጠው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ከሰብአዊ ነቢያት የሚበልጥ በመሆኑ ምክንያት ነው። እርሱ በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል ከተቀበሉትና እግዚአብሔር ራሱን አያሌ ጊዜያት ከገለጠባቸው ሰዎች ሁሉ በላይ ነው።

ሀ) የእግዚአብሔር *መንግሥት ወራሽ* የሆነውና እግዚአብሔር ወደ ዓለም የሚያመጣቸውን በረከቶች ሁሉ የሚቀበለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ ዙፋን ወራሽና አይሁዶች የሚጠብቁት *መሢሕ* ነው።

ለ) እግዚአብሔር አብ ነገሮችን ሁሉ ለመፍጠር ክርስቶስን ሾሟል።

ሐ) ክርስቶስ ሰው ብቻ ሳይሆን አምላክም ነው። እርሱም ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል የሆነ ክብር አለው። *የክብሩ መንጸባረቅና የባሕሪው ምሳሌ* በመሆኑ በሕልውናው፥ በባሕሪውና በተግባራቱ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብ ነው።

መ) ክርስቶስ *«ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ»* አጽናፈ ዓለሙን ጠብቆ ያኖረዋል።

ሠ) *ኃጢአታችንን የሚያነጻው* ክርስቶስ ነው።

ረ. ክርስቶስ *«በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀምጧል።»* ይህም የክብር ስፍራ ነው። በጥንታዊ ባህሎች፥ አንድ ንጉሥ በአዛዥነት ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን ባለሥልጣን (ብዙውን ጊዜ የራሱን ልጅ ወይም እንደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ያለውን ባለ ሥልጣን) ከቀኙ ያስቀምጠው ነበር። ምንም እንኳን በዋንኛው ሰማያዊ ዙፋን ላይ የሚቀመጠው እግዚአብሔር አብ ቢሆንም፥ የዚህ መልእክት ደራሲ ክርስቶስ ከሌሎች ኃይሎች ሁሉ ከፍ ብሎ በእግዚአብሔር አብ የሥልጣንና የአገዛዝ ቀኝ እንደሚቀመጥ ይናገራል።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፦ ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ አምላክ እንደሆነ የሚያሳዩበትን ሁኔታ አብራራ። ለ) ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩልና ዳሩ ግን የተለየ መሆኑን የሚያሳዩት እንዴት ነው? ሐ) እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ እንጂ የተለያዩ የሥላሴ አካላት አለመሆናቸውን የሚያስረዳውን «የኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ትምህርት የሚያፈርሱት እንዴት ነው? |

በአመዛኙ እንደ ሙሴና ሕዝቅኤል እግዚአብሔርን ለማየት በቻልን ብለን እናስባለን። ነገር ግን የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሙሴ ወይም ሕዝቅኤል ካዩበት በበለጠ እግዚአብሔርን በተሟላ መልኩ እንደገለጠው ያብራራል። ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «እኔን ያየ አብን አይቷል፤ እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ. 14:9-10) ብሏል። አሁን ክርስቶስን በሥጋዊ ዓይናችን ልናየው አንችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር አብ ክርስቶስን በወንጌላት ውስጥ ገልጦልናል። የሚያሳዝነው ብዙ ሰዎች በወንጌላት ውስጥ የእግዚአብሔር እጅግ የተሟላ መገለጥ በሆነው በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን አያዩትም። ብዙዎቻችን ሰዎች ስለ

ክርስቶስ ሲያወሩ ወይም ሰዎች በክርስቶስ ስም ተአምራትን ሲሠሩ ለማየት እንፈልጋለን። ወንጌላትን በጥንቃቄ የማናጠና ከሆነ በተግባራችን ለእግዚአብሔር አብ፥ «በእርግጥ በአንተ ደስተኞች አይደለንም፥ ግን አንተንና ባህሪህን፥ ፍቃድህን ለማወቅ አንፈልግም፥ ምክንያቱም ጊዜ ወስደን ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስን በቃልህ ውስጥ በተገለጠበት መልኩ ለማወቅ አንሻም» ማለታችን ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥናት እግዚአብሔር አብን በበለጠ ለማወቅ ምን እያደረግክ ነው? ለ) እግዚአብሔር አብና ወልድን በበለጠ ለማወቅ ልታደርግ የምትችላቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

2. ክርስቶስ ከመላእክት ይበልጣል (ዕብ. 1፡4-2፡18)

በአይሁዶች ባሕሪና እምነት ውስጥ መላእክት በከፍተኛ ደረጃ ይከበራሉ። አይሁዶች ታላቅ የእግዚአብሔር መገለጥ እንደሆነ የሚያምኑት የሙሴ ሕግ የተሰጠው በመላእክት በኩል ነበር (ዕብ. 2፡2)። ስለሆነም፥ አይሁዳውያን አማኞች ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ መረዳት ያስፈልጋቸው ነበር። የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስቶስ ከየትኛውም መልአክ የሚበልጥባቸውን መንገዶች እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡-

ሀ) ክርስቶስ ለየትኞቹም መላእክት ከተሰጠ ስም ወይም ማዕረግ የሚበልጥ ስም አለው። እርሱ የእግዚአብሔር «ልጅ» ተብሏል።

ለ) እግዚአብሔር መላእክት ክርስቶስን እንዲያመልኩ አዝዟቸዋል።

ሐ) መላእክት የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንጂ የሚመለኩ ወይም የሚከበሩ አይደሉም። ነፋስና እሳት ሰውን የሚያገለግሉ ነገሮች እንደሆኑ ሁሉ (በነፋስ የሚሠራ ወፍጮ ለማሰንሣት፥ ምግብ ለማብሰል፥ ወዘተ...)፥ መላእክትም የተፈጠሩት እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ እና ዕቅዱን እንዲፈጽሙ ነው።

መ) የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ክርስቶስ አምላክ ነው። አምላክ እንደ መሆኑ መጠን፥ ዙፋኑ ዘላለማዊ ነው። በዚሁ የዘላለም መንግሥት ውስጥ በሰዎች ሁሉ ላይ የመግዛት ሥልጣን አለው። እርሱ ከእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ በላይ ነው። ይህም መላእክትንና ሰዎችን ይጨምራል።

ሠ) ክርስቶስ ዘላለማዊ ነው። አርጅቶ ከሚሞትና በአንድ ቀን ከሚጠፋ ፍጥረት በተቃራኒ፥ ክርስቶስ ለዘላለም አይለወጥም። ከዚህ በተቃራኒ መላእክት ፍጡራን በመሆናቸው ጅማሬ አላቸው።

ረ) ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ የሥልጣን ሥራ ተሰጥቶታል። ይህ የክብር ስፍራ ከክርስቶስ በቀር ለመላእክት አልተሰጠም።

ደራሲው ለአይሁዳውያን አማኞች ክርስቶስ እንዴት ታላቅ እንደሆነ እያሳያቸው ነው። በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ያሉትን እንደ መላእክት ያሉትን ታላላቅ የተፈጠሩ ነገሮች በመውሰድ ከክርስቶስ ጋር ያነጻጽራቸዋል። መላእክት ታላቅ ሥልጣን ቢኖራቸውም፥ ክርስቶስ አምላክ በመሆኑ ይበልጣቸዋል። ስለሆነም፥ አይሁዶችና እንደ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ያሉ ሰዎች መላእክትን ማክበር ቢኖርባቸውም፥ ከክርስቶስ ጋር ሲነጻጸሩ ግን

እጅግ ዝቅተኛ ስፍራ እንዳላቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል። መመለክ የሚገባው ኢየሱስ ነው፤ መልአክን በፍጹም ማምለክ የለብንም።

ከዚያም ደራሲው ሌላ አስደናቂ እውነት ይገልጻል። በመላእክትና በክርስቲያኖች መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? ክርስቲያኖች ለመላእክት ልዩ ክብር መስጠት ይገባቸዋል? ወደ መላእክት መጸለይ አለብን? ልናመልካቸው ይገባል? ደራሲው በአይሁዳውያን አስተሳሰብ እነዚህን ጥያቄዎች በማንሣት፥ መላእክት «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚያገለግሉ መናፍስት አይደሉምን?» ሲል ይጠይቃል። ምንም እንኳን መላእክት ታላቅና ኃያል ቢሆኑም፥ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር መንፈሳዊ አካል የሆኑ ክርስቲያኖች ከመላእክት ይበልጣሉ። መላእክት እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማስፈጸም የሚጠቀምባቸው አገልጋዮች ናቸው። እግዚአብሔር ልጆቹን (አማኞችን) እንዲያገለግሉ መላእክትን ይጠቀማል።

25ኛ ጥያቄ፡- ይህ ምንባብ መላእክት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግንና እነርሱን ለማምለክ መሻትን በተመለከተ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው እንዴት ነው?

## (የመጀመሪያው የማስጠንቀቂያ ምንባብ – ዕብ. 2፡1-4)

ደራሲው ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ ማስተማሩን አቋርጦ የመጀመሪያውን ዐቢይ የማስጠንቀቂያ ምንባብ ያቀርባል። ይህ የጎንዮሽ ጉዳይ በማቅረብ የመጽሐፉን አሳብ የሚያቋርጥ በመሆኑ፥ ምሁራን ቅንፋዊ ሲሉ ይገልጹታል። ከዕብራውያን መልእክት ደራሲ ዐበይት ዓላማዎች አንዱ የአይሁድ አማኞችንና ክርስቲያኖችን በሙሉ ከእምነት ተሰናክለው እንዳይወድቁ ማስጠንቀቅ ነው። እያንዳንዱ የማስጠንቀቂያ ምንባብ ካለፈው ይበልጥ እየጠጠረ ይሄዳል።

26ኛ ጥያቄ፡- ዘጸ. 19፡1-25፤ 20፡18-21 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ለአይሁዶች ሕግ ለመስጠት በሲና ተራራ ላይ በተገለጸበት ወቅት ሁኔታው ምን ይመስል እንደነበር ግለጽ። ለ) አይሁዶች ይህን ያህል የፈሩት ለምን ነበር? ሐ) ከፍርሃታቸው የተነሣ ሙሴ ምን እንዲያደርግ ለመኑት?

ስለ መላእክት ማስተማሩ ደራሲው ሕግ በመላእክት አማካኝነት በእስራኤላውያን ስለተሰጠበት ሁኔታ እንዲያስብና የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ልጅ ለሰው ልጆች ከገለጸበት ሁኔታ ጋር እንዲያነጻጽር አደረገው። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ክርስቶስ ከመላእክትና ከሙሴ እንደሚበልጥ ሁሉ፥ ክርስቶስ ያመጣው በጸጋ የሚገኝ የመዳን መንገድም እንዲሁ መላእክት ለአይሁዶች ካመጡት የሕግ መንገድ ይበልጥ ነበር (ዘዳግ. 33፡2)። አይሁዶች ሁሉ የሕጉን መሰጠት በታላቅ አድናቆት ነበር የሚያስታውሱት። ቅዱሱ እግዚአብሔር ከመላእክት ጋር ፍጹም ሕጉን ምርጥ ሕዝብ ለሆኑት አይሁዶች ሰጥቷል። ይህ ጊዜ ምን ያህል ልዩ እንደ ነበር መመልከት ይቻላል። አይሁዶች ሁሉ ለዚሁ የሕግ መሰጠት ራሳቸውን ማንጻት ያስፈልጋቸው ነበር። እነርሱም ሆኑ እንስሶቻቸው ወደ

ተራራው ቢጠጉ ሞት እንደሚጠብቃቸው ተነግሯቸው ነበር። የእግዚአብሔር የሕልውናው ክብር እጅግ ታላቅ በመሆኑ እስራኤላውያን በፍርሃት ተዋጡ። ከዚህም የተነሣ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ ጠየቁት። ሕጉ እራሱ የጠነከረ በመሆኑ፥ ከዚሁ የሕግ ክፍሎች አብዛኞቹን መተላለፍ የሞት ቅጣት ያስከትል ነበር (ለምሳሌ፥ ዘጸ. 31፡14፤ 21፡12-17፥ ዘሌዋ. 20፡10-11)። በመሆኑም የብሉይ ኪዳን የሕግ መንገድ አለመቀበሉ ታላቅ ቅጣት ያስከትል ነበር።

ስለሆነም፥ በተፈጠሩ መላእክት አማካኝነት የተሰጠው ዝቅተኛው የብሉይ ኪዳን ሕግ ተላላፊዎችን በሞት የሚያስቀጣ ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣው የእግዚአብሔር የጸጋ መንገድ በማይቀበሉት ሰዎች ላይ የበለጠ ቅጣት ያስከትል ነበር። ይህም በእግዚአብሔር ልጅ በኩል መምጣቱ ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለአይሁዶች በተለያዩ ተአምራቶች ያረጋገጠው መገድ ነው። (እግዚአብሔር ተአምራትን ስለሚልክባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው። ተአምራቶች የሚመጡት የሰዎችን ፍላጎት ብቻ ለማሟላት ሳይሆን ወንጌሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለማረጋገጥ ጭምር ነው።) በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎች መስጠታቸው ወንጌሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን ያመለክታል። ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ያልነበረ ልምምድ ነው። ይህንን ሁሉ ችላ ብሎ ዝቅ ወዳለው የሕግ መንገድ መመለሱ የበለጠ ቅጣት ያስከትል ነበር። ይህም ሥጋዊ ሞት ብቻ ሳይሆን፥ መንፈሳዊና ዘላለማዊ ሞት ጭምር ነው።

ስለሆነም፥ ደራሲው ራሱን ጨምሮ አማኞች ሕይወታቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ያስጠነቅቃል። ክርስቲያኖች ከወንጌሉ እውነት እንዳይወድቁ ያስጠነቅቃቸዋል። ብዙ ጊዜ አለማመን በድንገት የሚከሰት ነገር ሳይሆን በሂደት የሚመጣ ነው። ይህ መልሕቋ ተሰብሮባት ወደ ውኃ እንደምትሰምጥ እና ከዚያም ከድንጋይ ጋር እንደምትጋጭ ጀልባ ማለት ነው። ወይም ደግሞ የታሰረበትን ገመድ በጥሶ ወደ ጫካው ውስጥ በመሮጥ ጉድጓድ ውስጥ እስኪገባ ድረስ በሚንከራተት በጓላም የአውሬ ራት እንደሚሆን በግ ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ደራሲው ወደ ሐሰት ትምህርት የምንገባውና ባለማመን ልባችን የሚደነድነው ቀስ በቀስ እንደሆነ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና ሳናቋርጥ መጸለይ እናቆማለን። ከዓለማውያን ጋር ወዳጅነት እንመሠርታለን። ገንዘብ ወይም ትምህርት ዋነኛው ነገር እንደሆነ በማሰብ በእነዚሁ ነገሮች ላይ እናተኩራለን። ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ እናቆማለን። ዓይኖቻችን ሴቶችን በምኞት ይመለከታሉ። ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር ቢራ መጠጣት እንጀምራለን። እነዚህ ሁሉ ነገሮች መንፈሳዊ ሕይወታችን እንዲጎዳ ያደርጋሉ። በመጨረሻም፥ የእምነታችን መሠረት ይናጋና እምነታችን ይደረመሳል።

27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እምነቱን ስለካደ እና በግል ስለምታውቀው አንድ ሰው አስብ። ከህደታቸው እምነታቸውን ባለመጠበቃቸው ምክንያት ቀስ በቀስ የጀመረው እንዴት ነበር? ለ) ባለማመን እንዳትወድቅ በሕይወትህ ምን እያደረግክ ነው?

ደራሲው ክርስቲያኖች ባለማመን እንዳይወድቁ በጽኑ ካስጠነቀቃቸው በኋላ፥ ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ የሚያስረዳውን ትምህርት ይቀጥላል።

ሠ) ክርስቶስ ሰው በመሆኑ ከመላእክት ይበልጣል (ዕብ. 2፡5-9)። ደራሲው ስለ ሁለት ዓይነት ሰዎች የሚያስብ ይመስላል። በመጀመሪያ፤ ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ። ምንም እንኳን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፥ ሰው ሆኗል። ይህ ማለት ግን በሥልጣንና ኃይል ከመላእክት በታች ሆኗል ማለት አይደለም። ክርስቶስ ሰው መሆኑ፥ የመግዛት መብቱን ከመቀነስ ይልቅ በምድር ላይ በመሢሕነቱ እንዲገዛ አስችሎታል። ይህ ሰው ከመሆኑ በፊት የሚቻል አልነበረም። ይህ ደግሞ ለየትኛውም መልአክ ያልተሰጠ መብት ነው።

ሁለተኛ፥ ዛሬ ክርስቶስን በታማኝነት ከተከተልነው አማኞች ሁላችንም በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ እንደምንገዛ ቃል ተገብቶልናል (2ኛ ጢሞ. 2፡12፤ ራእይ 5፡10)። ብዙውን ጊዜ መላእክት ከሰዎች እንደሚበልጡና አስፈላጊነታውም ከሰዎች በላይ እንደሆነ እናስባለን። ወደ እግዚአብሔር የቀረቡና ቅዱሳን ናቸው ብለን እንገምታለን። ኃጢአት አይሠሩም። የበለጠም ኃይል አላቸው። ስለሆነም ይበልጣሉ ብለን እናስባለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህ የተለየ አቋም አለው። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ መዝሙር 8፡4-6ን በመጥቀስ፥ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ሰዎች ከመላእክት እንደሚበልጡ ያስተምራል። በሚመጣው ዓለም ውስጥ ማለትም ወደፊት በሚመሠረት የክርስቶስ መንግሥት ውስጥ፥ እግዚአብሔር ለመላእክት የመግዛትን ሥልጣን አልሰጠም። ነገር ግን በምድር ላይ እና ወደፊት በሚመጣው መንግሥት ላይ የመግዛት ሥልጣን የተሰጠው ለሰዎች ነው። ምንም እንኳን የሰው ልጅ ከኃያላን መላእክት ጋር ሲነጻጸር ደካማ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የመግዛት ሥልጣን የተሰጠው ለሰው እንጂ ለመላእክት አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎችን በፈጠረ ጊዜ ምድርን እንዲገዙ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል (ዘፍጥ. 1፡26)። ነገር ግን ከኃጢአት የተነሣ የሰዎች አገዛዝ እግዚአብሔር እንዳሰበው ተግባራዊ አልሆነም። አንድ ቀን ግን ይህ ይለወጣል። የእግዚአብሔር ልጆች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረው ምድርን ይገዛሉ። ይህ አገዛዝ እግዚአብሔር መጀመሪያ ዓለምን ሲፈጥር ያቀደውን ውጥን ተግባራዊ ያደርገዋል።

ፍጹም ሰው የሆነው ክርስቶስ ቀድሞውኑ መግዛት ጀምሮአል። ምንም እንኳን ክርስቶስ በምድር ላይ የሚኖር ፍጹም ሰው፥ ለእግዚአብሔር የተገዛና በመስቀል ላይ የሞተ በመሆኑ ምክንያት ለጊዜው ከመላእክት አንሶ የነበረ ቢሆንም፥ ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ የሚያመለክቱ አያሌ ነገሮች ተፈጽመዋል፡-

ሀ) ክርስቶስ *የክብር ስፍራ* በሆነው በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል። ጳውሎስ እንደተናገረው፥ ክርስቶስ ከስሞች ሁሉ የሚበልጥ ስም ተሰጥቶታል (ፊልጵ. 2፡9-11)።

ለ) ክርስቶስ *ለሰዎች ሁሉ ሞትን ቀምሷል።* ክርስቶስ እምነታችንን በእርሱ ላይ በጣልን ሰዎች ምትክ በመሆን ለሥጋዊ እና መንፈሳዊ ሞት ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል። መንፈሳዊ ሞቱን ከእግዚአብሔር አብ መለየቱ ነበር። እኛ በሥጋ ልንሞት ብንችልም፥ መንፈሳዊ ሞት ግን አይገጥመንም። የዘላለም ሕይወት ይኖረናል።

ሐ) ክርስቶስ *የደኅንነት ምንጭ* ነው። በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት፥ የነገሮች ሁሉ ጀማሪ የሆነው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት ሰዎች ሁሉ መሠረት መሪ ነው። በግሪኩ «ደራሲ» (በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ጀማሪ ዕብ. 4፡10) የሚለው ቃል ከሰዎች ፊት እየቀደመ ጫካውን በመመንጠር መንገድ የሚያበጅንም ሰው ያመለክታል። በመሆኑም ክርስቶስ ከዚህ በፊት ያልነበረውን የደኅንነት መንገድ ለመክፈት የእግዚአብሔር መሣሪያ ሆኖ አገለገለ። ሰዎች ሁሉ (አይሁዶችን ጨምሮ) ደኅንነትን ከፈለጉ ክርስቶስ የከፈተውን መንገድ መከተል ይኖርባቸዋል።

ክርስቶስ ይሄንን የደኅንነት መንገድ ለመክፈት ብቁ የሆነው እንዴት ነው? ይሄንን በአምላክነቱ ሊያደርግ አይችልም ነበር። ክርስቶስ ይህን ተግባር ለማከናወን ሥጋና ደም የለበሰ ሰው መሆን ያስፈልገው ነበር። ሙሉ አዳኝና አማላጅ ሊሆን የሚችለው ሰው ሲሆን ብቻ ነበር። ስለ ላሞች ብዙ ልናውቅና ነገር ግን ሰዎች እንጂ ላሞች ባለመሆናችን ምክንያት ላሞችን በትክክል ልንረዳቸውና በገጠማቸው ችግር ብዙ ልንረዳቸው እንደማንችል ሁሉ፥ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት እግዚአብሔር በሰይጣን ቁጥጥር እና በራሳችን የኃጢአት ተፈጥሮ ሥር ታስረን የምንኖርበት የኀብአዊነት ሕይወት ምን እንደሚመስል በትክክል ሊረዳ አይችልም ነበር። መሞት ማለት ምን ማለት እንደሆነም ከራሱ ገጠመኝ ተነሥቶ ሊያውቅ አይችልም ነበር። ፍጹም አምላክ የነበረው ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ ግን ይህ ሁሉ ተለወጠ። እርሱ ሙሉ በሙሉ ከሰዎች ጋር ራሱን አስተባበረ ስለሆነም ክርስቶስ ሰው ሆኖ መኖር ምን እንደሚመስል ከራሱ ገጠመኝ ሊያውቅ ይችል ነበር። ድካም ተሰምቶታል፤ ተፈትኗል፥ በሽታ፥ ድህነትና ሞት ሁሉ ተፈራርቀውበታል። እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ በሕይወት ገጠመኝነት የማያውቃቸው ነበሩ። በመሆኑም፥ ክርስቶስ ከአምላክነቱ ሊያደርግ የማይችለውን ተግባር ለመፈጸምና የበለጠ ብቁ አማላጅና አዳኝ ለመሆን ችሏል። ለሰው ልጆች ኃጢአት የሞተ ሰብአዊ-መለኮታዊ አካል በመሆኑ፥ ዲያቢሎስ በሰዎች ዘላለማዊ ዕድል ፈንታና ነፍሳት ላይ የነበረውን ቁጥጥር አስወግዷል። ክርስቶስ የኃጢአታችንን ዋጋ ስለከፈለ፥ የእርሱን ይቅርታ መንገድ ተቀብላለች፥ ለደኅንነታችን በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ ሰይጣን ሞት የሚገባን ኃጢአተኞች መሆናችንን በመግለጽ ሊከስሰንና ወደ መንፈሳዊ ሞት ሊመራን አይችልም።

ለ) ክርስቶስ ሰዎች ከአዳምና ሔዋን ዘመን ጀምሮ ሲፈሩ የነበሩትን የሞት ፍርሃት ባርነት አስወግዷል። ሞት ክርስቶስ ከሙታን እስከተነሣበት ጊዜ ድረስ ገዝቷል። ሃብታም፥ ዝነኛ፥ ኃያላን ወይም መንፈሳዊ የነበሩ ሰዎች በሙሉ ሞተዋል። የሰው ልጅ ይህን የሞት አደጋ ሊያስወግድ የሚችልበት ምንም መንገድ የለም። ክርስቶስ በሞተና በተነሣ ጊዜ ግን የእግዚአብሔር

ልጆች ከሞት በኋላ ምን እንደሚሆኑ የሚያመለክት ተግባር አከናውኗል። የሞትን ፍርሃት በማስወገድ ከእግዚአብሔር ልጆች ላይ የሞትን መውጊያ አንሥቷል። እርሱ የትንሣኤ ሙታን ማረጋገጫችን ነው።

ሐ) እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ኃጢአተኛ ለሆኑት ለሰው ልጆች የበለጠ ርኅራኄ እና እገዛ ሊያደርግላቸው ይችላል። ቀደም ሲል ይህንን ለማድረግ አልቻለም ነበር። ደራሲው እንዳለው «እርሱ እራሱ ተፈትኖ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።» እግዚአብሔር በሥጋው መከራ ተቀብሎ አያውቅም። በመሆኑም፥ እኛ መከራ በምንቀበልበት ጊዜ ከራሱ ገጠመኝ ተነሥቶ ሊራራልን አይችልም ነበር። ክርስቶስ ሰው ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ለኃጢአት የምንፈተንበትን ሁኔታ ወይም ሞትን እንዴት እንደምንፈራ ለመረዳት ነበር። ክርስቶስ ሰው ከሆነ በኋላ ታላቅና ኃያል አምላክ ብቻ ሳይሆን፥ ችግሮቻችን የሚረዳ ሰው ለመሆን ችሏል። እርሱ ልክ እንደኛ ሆነ። የዕብራውያን ጸሐፊ እንደሚለው፥ ምንም እንኳን ክርስቶስ ፍጹም ቅዱስ እና ኃጢአት የሌለው ቢሆንም፥ ክርስቶስ አሁን ፍጹም ሆኗል። በዚህ ስፍራ «ፍጹም» የሚለው ቃል ክርስቶስ ቀደም ሲል ኃጢአተኛ እንደነበረና አሁን ግን ኃጢአት እንደሌለው የሚያመለክት አይደለም። ነገር ግን ክርስቶስ አሁን ሙሉ ለሙሉ የሰው ልጆች የደኅንነት ምንጭና ሊማልድላቸው የሚችል ሊቀ ካህን ለመሆን እንደቻለ የሚያመለክት ነው።

ሰዎች እንደ ሙሴ ወይም ማርያም ያሉ አማላጆች ያስፈልጉናል ከሚሉባቸው ምክንያቶች አንዱ እግዚአብሔር ሩቅ እንደሆነና ያሉበትን ሁኔታ እንደማይገነዘብ ወይም ለመገንዘብ እንደማይፈልግ በማሰባቸው ነው። የዕብራውያን መልእክት ግን ይህ እውነት እንዳልሆነና አማላጆች እንደማያስፈልጉን ይናገራል። አምላክ ብቻ ሳይሆን ፍጹም ሰው የሆነ አዳኝ አለን። አሁን እንኳን በሰማይ እያለ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው። ሰው እንደ መሆኑም ከፈተና ጋር መታገል ምን እንደሆነ ያውቃል። ክርስቶስ ስደትንና ሞትን መፍራት፥ እምነትን ለመካድ መፈተን ምን እንደሆነ ያውቃል። ድህነት፥ ከጓደኞችና ቤተሰቦች ዘንድ ተቀባይነትን ማጣት፥ ወዘተ... ምን እንደሆነ ያውቃል። ክርስቶስ የምንጋፈጣቸውን ነገሮች ሁሉ ስለሚያውቅ፥ እነዚህ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ እንደሚረዳንና እንደሚያግዘን በማወቅ በልበ ሙሉነት ወደ እርሱ ልንነሣ እንችላለን።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አማኞች እንዲፈሩና እምነታቸውን እንዲክዱ የሚያደርጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ለ) ክርስቶስ እንዴት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እንዳለፈ ግለጽ። ሐ) በመጋፈጥ ላይ ያለነውን ችግር ቀደም ሲል ተጋፍጦ ያለፈና ሊረዳን የሚፈቅድ ክርስቶስ ከሰማይ እንዳለ ማወቁ ለምን እንደሚያበረታታንና እንደሚያስፈልገን ግለጽ። |

መ) ክርስቶስ *«ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት»* ሆነ። ይህ ከዕብራውያን መልእክት ዐበይት ትምህርቶች አንዱ በመሆኑ ወደ በኋላ ሠፋ አድርገን እንመለከተዋለን። የዕብራውያን ጸሐፊ ኃጢአተኛ፥ ጊዜያዊና ሊረዳን ከማይችል የአይሁድ ሊቀ ካህናት በተቃራኒ፥ የሚያውቀን፥ ስለ እኛ የሚገደውና ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት

የሚረዳን ሊቀ ካህናት በሰማይ እንዳለን ያስረዳል። ክርስቶስ ሊቀ ካህናታችን ለመሆን ይችል ዘንድ ከኃጢአት በቀር ሰብአዊ ልምምዶችን ሁሉ አደረገ። ካልሆነማ፥ በእግዚአብሔር አብ ፊት እንዴት በብቁ ሁኔታ ሊማልድልን ይችል ነበር?

ሠ) ክርስቶስ ራሱን በመስቀል ላይ በመሠዋት፥ *«ለሕዝብ ኃጢአት ለማስተሰረይ»* ቻለ። ስርየት የሚለው ቃል ከብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት ሥርዓት የመጣ ነው (ዘሌዋ. 17፡11፤ 16፡20–22 አንብብ።) የቃሉ ትርጉም ኃጢአትን በመሸፈን የእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት ከሰው ላይ እንዳይደርስ መከላከልን ያመለክታል። እግዚአብሔር ለሰው ኃጢአት የሚሰጠው ፍርድ በምትክነት መርሕ ተግባራዊ ይሆን ነበር። በግለሰቡ ፋንታ አንድ እንስሳ እንዲሞት ይደረጋል። የእንስሳው ደም በሚረጭበት ጊዜ የግለሰቡን ኃጢአት ስለሚሸፍን ሰውየው ከእግዚአብሔር ፍርድ ይተርፋል። (ደራሲው ወደ በኋላ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ወቅት ከእንስሳት ደም የበለጠ የኃጢአት መሸፈኛ እንደተገኘ ያብራራል።) ኢየሱስ በእኛ ምትክ ስለሞተ እና ደሙ ኃጢአታችንን ስለሚሸፍን፥ እግዚአብሔር ይቅር ሊለንና ፍርዱን ከእኛ ላይ ሊያነሣ ይችላል። ጳውሎስ እንዳለው፥ «በክርስቶስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8፡1)።

ረ. ክርስቶስ *ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ያመጣል።* ደራሲው ይህን የሚለው የደኅንነትን የመጨረሻ ጫፍ በመመልከት ነው። ይህ ክርስቶስ ለልጆቹ በሚመለስበት ጊዜ የሚከናወን ተግባር ይሆናል። በእርሱ የምናምን ሁላችን ከሞት እንነሣና አዲስ አካል እንለብሳለን። ከዚያም በክብር በእግዚአብሔር ፊት እንቆማለን።

> 29ኛ ጥያቄ፡– የሚማልድልህ ሰውና አምላክ የሆነ አዳኝ በሰማይ መኖሩ የሚያበረታታህ ለምንድን ነው? አሁን አምላክና ሰው የሆነው ስላደረገልህና እያደረገልህ ስላለው ነገር ለማመስገን ጊዜ ውሰድ።

## ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል (ዕብ. 3፡1–19)

ደራሲው ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥና ሰብአዊ ባህሪን በመልበሱ ምክንያት ሙሉ በሙሉ እንደሚረዳን ከገለጸ በኋላ፥ አማኞች *(ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋይ የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች)* ወደ ክርስቶስ እንዲመለከቱ ይጋብዛል። (ማስታወሻ፡– ዕብ. 3፡1 እንደ «ስለዚህ» ዓይነቶቹን ቃላት በትኩረት መመልከቱ ክፍሉን መረዳታችንን ለማረጋገጥ ጥሩ ምሳሌያችን ነው። ስለዚህ የሚለው ቃል ቀደም ሲል ከተገለጸው እውነት የተነሣ አንድ ልንሰጥ የሚገባን ምላሽ እንዳለ ያመለክታል።) አይሁዶች እርዳታ ፍለጋ ወደ መላእክት መሄድ አያስፈልጋቸውም ነበር። ክርስቲያንና የፖለቲካ መሪዎች የሆኑትን ሰዎችን መፈለግ አያስፈልጋቸውም። ስመ ጥር ወደሆኑ ሰዎች መልስ ፍለጋ መሄድ አያስፈልጋቸውም ነበር። ማየት የሚያስፈልጋቸው ክርስቶስን ብቻ ነበር።

ሀ. ሐዋርያ፡– ከእርሱ በበለጠ አካል በውክልና እንዲሠራለት የሚላክ አገልጋይ ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሙሉ ሥልጣን ይዞ ነበር የተላከው። ወደ ምድር የመጣው፥ የተናገረውና ያደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር

ፋንታ የተከናወነ ነበር። ስለሆነም ክርስቶስ የተናገረው ወይም ያስተማረውን አለመቀበል ማለት እግዚአብሔር አብን እንዳለመቀበል ማለት ነው። አይሁዶች፥ «እግዚአብሔር አብን እንደ አያት ቅድማያቶቻችን እናመልከዋለን እያሉ ክርስቶስ ግን አንፈልገውም» ሊሉ አይችሉም ነበር። ምክንያቱም ክርስቶስን ባለመቀበል እግዚአብሔር አብንም እየተቃወሙ ነበርና።

ለ) ሊቀ ካህናት፡- የአይሁዶች የአምልኮ ሥርዓት የሚመራው በሊቀ ካህናት ነበር። ሕህዝቡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ያገኙ ዘንድ የኃጢአት መሥዋዕቶችን የሚያቀርበው እርሱ ነበር። ነገር ግን ደራሲው የተሻለ መሥዋዕት ያቀረበ (ራሱን) ሌላ የሚበልጥ ሊቀ ካህናት እንዳለ ያመለክታል። የክርስቶስን መሥዋዕት ትቶ ሰብአዊ ሊቀ ካህናት ወደሚያቀርበው የእንስሳት መሥዋዕት መመለሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከእንግዲህ ይቅርታ አያስገኝም ነበር።

አይሁዶች፥ «ክርስቶስ ከመላእክት ሊበልጥ ይችላል ነገር ግን በሲና ተራራ ሕግን ከሰጠን ከሙሴ ሊበልጥ አይችልም» ማለታቸው አይቀርም ነበር። ስለሆነም የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስቶስ ከሙሴ እንደሚበልጥ ወደሚናገርበት ሦስተኛ ነጥቡ ይሸጋገራል። በአይሁዶች አስተሳሰብ ከሙሴ የሚበልጥ ሰው አልነበረም። ሙሴ ከግብጽ ባርነት ነፃ አውጥቷቸው ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን እንዲያደርጉና ሕግም እንዲቀበሉ አድርጓል። ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ተነጋግሯል። ምንም እንኳን አብርሃምና ዳዊት ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ቢሆኑም፥ ሙሴን የሚያህል አልነበረም። (አይሁዶች እንደ ብዙዎቻችን በሰው ላይ ትኩረት በማድረጋቸው አንድን ነገር ለማድረግ የሚያስፈልግ እውነተኛው ኃይል ከየት እንደሚመጣ ዘንግተው ነበር። እስራኤላውያንን ከግብጽ ያወጣው እግዚአብሔር እንጂ ሙሴ አልነበረም።) ሕግንና ቃል ኪዳንን የሰጠው እግዚአብሔር እንጂ ሙሴ አልነበረም። በተመሳሳይ መንገድ ለሰዎችም ደኅንነት የሚሰጠው እግዚአብሔር እንጂ እኛ አይደለንም። በአምልኮ፥ በዝማሬና በቃል፥ በስብከት ውስጥ የሚንቀሳቀሰው እግዚአብሔር እንጂ ኳየሩ ወይም ሰባኪው አይደለም።

የዕብራውያን ጸሐፊ ሙሴ ከክርስቶስ ይበልጣል ለሚለው የአይሁዶች አስተሳሰብ መልስ ለመስጠት፥ ሙሴንና ክርስቶስን ያነጻጽራል።

ተመሳሳይነታቸው፡ ሀ) ሙሴና ኢየሱስ 1) ሁለቱም ለእግዚአብሔርና ለተሰጣቸው ሥራ ታማኞች ነበሩ። (ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ማውጣት ኃላፊነት ሲሰጠው፥ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከመንፈሳዊ ባርነት ነፃ የማውጣት ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር።) ለ) ሁለቱንም ለአገልግሎት የሾማቸው እግዚአብሔር ነበር። ራሳቸው አገልግሎቱን አልመረጡም።

ልዩነቶቻቸው፡ ክርስቶስ በሚከተሉት ምክንያቶች ከሙሴ ይበልጣል ምክንያቱም፡-

ሀ) ሙሴ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ነበር (የእግዚአብሔር ቤተሰብ)። ሙሴ አይሁዳዊ በመሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት የብሉይ ኪዳን አይሁዳውያን ቤተሰብ ነበር። ክርስቶስ ግን አምላክ እንደ መሆኑ፥

የቤቱ ማለትም የእግዚአብሔር ሕዝብ አናጺ ነበር። የብሉይ ኪዳንንም ሆነ የአዲስ ኪዳንን ሕዝብ የመሠረተው ክርስቶስ ነበር።

ለ) ሙሴ በቤቱ ውስጥ (የአይሁድ ሕዝብ) የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር። እርሱም ወደፊት የሚመጣውን ታላቅ ቤት አመልክቷል። ክርስቶስ ለዘላለማዊ ቤት (በእግዚአብሔር ሕዝብ) ላይ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ምንም እንኳን ሙሴ ታላቅ፥ የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም፥ አይሁዳውያን አማኞች ሙሴ ሰው መሆኑን መገንዘብ ነበረባቸው። ሰው ደግሞ መመለክ የለበትም። ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገነባ አምላክ ነው። ደኅንነትን ፍለጋ ወደ ሕግና ሙሴ መመለሱ ከአምላክ ወደ ሰው የመመለስ ያህል ነበር።

| |
|---|
| 30ኛ ጥያቄ፡- እኛም ክርስቶስን ከማመን ሰውን ወደ ማመን እንዴት ልንመለስ እንደምንችል ግለጽ። ይህ የተሳሳተ የሚሆነው ለምንድን ነው? |

## ሁለተኛ የማስጠንቀቂያ ምንባብ - ዕብ. 3፡7–4፡13 [ክርስቶስ ከኢያሱ ይበልጣል (ዕብ. 4፡1–13)።]

ብዙውን ጊዜ ስላለፈው ዘመን ታላቅነት ለማውራት እንወዳለን። ቤተ ክርስቲያናችን እንዴት እንደ ተመሠረተችና እንዳደገች፥ እግዚአብሔር በመካከላችን የሠራቸው ተአምራት፥ ወዘተ... ተናግረን አንዘልቅም። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ አይሁዶች የሙሴን ዘመን ታሪኮች ቀይ ባህርን ስላቋረጡባቸው ተአምራታዊ ሁኔታዎች ያስታውሱ ነበር። መናውን፥ ከዓለት ውስጥ የፈለቀውን ውኃ፥ ድርጭቱን እግዚአብሔር ለሕዝቡ አስደናቂ ነገር እንደሠራበት ዘመን አድርገው ይቆጥሩ ነበር። የአይሁዶችን ታላቅ ሕዝብነት ለመግለጽ ኃላፊ ታሪኮች ይጠቅሱ ነበር። ይሁንና የታሪኩን ሌላኛ ጎን ዘንግተው ነበር። ይኸውም የአይሁድን ሕዝብ ዐመፅና እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ የነበራቸውን እምነት በማጣታቸው ምክንያት ያመጣባቸው ፍርድ እንዳልተፈጸመ ታሪክ ማለፋቸው ነበር። የዕብራውያን ጸሐፊ የተቀረውን የሙሴን ታሪክና በአባቶቻቸው ላይ የደረሰውን ሁኔታ ሊያስታውሳቸው ፈለገ። እግዚአብሔር በሠራላቸው ተአምራት ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ ደራሲው በእግዚአብሔር ላይ እምነታቸውን ጥለው ቢሆን ኖሮ ምን ሊከሰት እንደሚችል ይገልጽላቸዋል።

በዚህ በሁለተኛው የማስጠንቀቂያ ምንባብ ደራሲው ወደ ከነዓን በመግባቱ «እረፍት» ላይ አጽንኦት ይሰጣል። ደራሲው ወደ ከነዓን የመግባቱን እረፍት ደኅንነትን ከማግኘትና ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመግባቱ እረፍት ጋር ያነጻጽራል። ምሁራን ይህ እረፍት የሚያመለክተው አማኞች በምድር ላይ ያገኙትን በረከት ስለመሆኑ ይከራከራሉ። ምናልባትም ይህ እረፍት በክርስቶስ የሚገኘውን የደኅንነት እረፍት (ከነዓንን ሳይሆን) በመንግሥተ ሰማይ የምናገኘውን ክብር አጣምሮ የያዘ ሳይሆን አይቀርም።

በብሉይ ኪዳን፥ አይሁዶች ከሙሴ መሪነት ከግብጽ እስከ ከነዓን የተጓዙበት መንገድ ጥቂት ሳምንታትን ብቻ የሚፈጅ ነበር። ነገር ግን ለአይሁዳውያኑ አርባ ዓመታት ፈጀባቸው። ከለማመናቸው የተነሣ፥ በምድረ

በዳ ውስጥ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ተአምራት የተመለከቱት ከሃያ ዓመት እድሜ በላይ የሆኑ አይሁዶች (ከኢያሱና ካሌብ በስተቀር) ወደ ከነዓን ምድር እረፍት ሳይገቡ ሞተዋል። በኢያሱ መሪነት ጊዜም አይሁዶች ወደ ከነዓን ሊገቡና ከአገሪቱ የተወሰነውን ክፍል ሊይዙ ቢችሉም፥ እግዚአብሔር ሊሰጣቸው የፈለገውን እረፍት አላገኙም ነበር። ባለማቋረጥ ከጠላቶቻቸው ጋር ጦርነት ይገጥሙ ነበር። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር ጋር አይጓዙም ነበር። ከዚህም የተነሣ በኋላ ከዚህች አገር በምርኮኛነት ተወስደዋል። አይሁዶች ከቶውንም እግዚአብሔር ሊሰጣቸው የፈለገውን መንፈሳዊና ሥጋዊ እረፍት አላገኙም። ለዚህም ምክንያቱ በእምነታቸው ሊጸኑና ለእግዚአብሔር ታማኞች ሆነው ሊኖሩ አለመቻላቸው ነው። ይህ እግዚአብሔር ለአይሁዶች ተስፋ የገባው እረፍት ገና ያልተፈጸመና ወደፊት የሚመጣ መሆኑን በመዝሙር 95:7-11 ውስጥ ተገልጾአል። የኢያሱ ዘመን ካለፈ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ የተጻፈው ይኸው መዝሙር፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ እረፍቱን ለማግኘት በእግዚአብሔር ታማኝነት ሊጸና እንደሚገባ ያሳስባል።

የአይሁድ ክርስቲያኖች፥ እንዲሁም ዛሬ በሕይወት ያለን ሁላችንም እግዚአብሔር ለእኛ ወዳዘጋጀው ወደዚሁ መንፈሳዊ የደኅንነት እረፍትና መንግሥተ ሰማይ እንድንገባ ተጠይቀናል። ነገር ግን ወደዚሁ እረፍት ለመግባት እንደ ቀድሞዎቹ አይሁዶች መሆን የለብንም። ልክ እንደ እነርሱ እግዚአብሔር እረፍቱን እንዳዘጋጀልን የተስፋ ቃል ሰጥቶናል። እንደ እነርሱ ወንጌሉን ሰምተናል፥ ልክ እንደ እነርሱ፥ የእግዚአብሔርን ተአምራት አይተናል። እረፍቱን ማግኘታችን ወይም አለማግኘታችን የሚወሰነው በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነትና ለእርሱ ታማኞች በመሆናችን ነው። ካላመንን ግን ዛሬ ምንም ያህል በረከቶች ብናገኝም፥ የኋላ ኋላ በአለማመናችን የተነሣ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንቀበላለን። ስለሆነም፥ *«እንደዚያ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ እረፍት ለመግባት እንትጋ»።* በመጀመሪያ፥ መንፈሳዊ እረፍታችንን ልንጀምር የምንችለው እንደ ይሁዲነት ባለ ታሪካዊ ሃይማኖት ወይም የወላጆቻችንን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እምነት በመከተል ሳይሆን፥ በክርስቶስ በማመን መሆኑን ሊታወስ ይገባል። ከክርስቶስ ፊታችንን በምንመልስበት ጊዜ ወደ እረፍቱ ለመግባት አልፈለግንም ማለት ነው። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔርን ሆን ብለን ሳንታዘዝ ስንቀርና በክርስቶስ ላይ የነበረንን እምነት ስንክድ፥ ይህ የዘላለማዊውን የመንግሥተ ሰማይ እረፍታችንን ከአደጋ ላይ ይጥላል። እግዚአብሔር ለአሁንና ለወደፊት የገባልንን መንፈሳዊና ዘላለማዊ እረፍት እናገኝ ዘንድ ለእግዚአብሔር ታማኝነት ጸንተን ስደትን ልንጋፈጥ ይገባል።

31ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ሰዎች ወደ ዓለም ወይም ወደ ቀድሞው ሃይማኖታቸው በሚመለሱበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያዘጋጀውን እረፍት የሚገፉት እንዴት ነው? ለ) የመንግሥተ ሰማያትን ዘላለማዊ እረፍት በተመለከተ፥ እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ የሚያስከትለው ዘለቄታዊ ውጤት ምንድን ነው?

ደራሲው ሁለተኛ ማስጠንቀቂያውን ወደ እግዚአብሔር ቃል በማመልከት ይፈጽማል። ሁላችንም ከምንጋፈጣቸው እጅግ አደገኛ ነገሮች መካከል

ከእምነታችንና ከታዛዥነታችን መውደቅ ይገጥሙናል። መውደቅ በምንጀምርበት ጊዜ፥ ብዙውን ጊዜ በልባችን ውስጥ ምን እየተፈጸመ እንዳለ መመልከቱ አዳጋች ነው። አእምሮአችን ወደ ተሳሳተ ትምህርት ወይም አስተሳሰብ እንዴት እየገሰገሰ እንዳለ አንገነዘብም። ፍላጎታችን እግዚአብሔር ወደማይከብርባቸው ነገሮች እየተሯሯጠ መሆኑን አንመለከትም። በኃጢአት በምንወድቅበት ጊዜ እንኳን ብዙውን ጊዜ አእምሮአችን ለፈጸምነው ጥፋት ማመኻኛ ለማግኘት ይሞክራል። ለመሆኑ ለዚህ ዓይነቱ ችግሮች መፍትሔው ምንድን ነው? የራሳችንን ልብ እንድንመለከት የሚረዳን ምን ይሆን? የዚህ መልእክት ደራሲ መፍትሔው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ መሆኑን ይጠቁማል። በሆስፒታል ውስጥ የበሽተኛውን ሰውነት ቀዶ ከውስጡ የተበላሸውን ነገር እንደሚያይና እንደሚያስወግድ ሐኪም የእግዚአብሔር ቃልም ከስለታም ሰይፍ በበለጠ ሁኔታ ወደ ሰው ልብ ይዘልቃል። የእግዚአብሔር ቃል እጅግ ጠልቆ ወደ ነፍሳችን ውስጥ ይዘልቃል። ይህም ብዙውን ጊዜ ሌሎችና ከራሳችንም የተደበቀ ስፍራ ነው። በዚያም የእግዚአብሔር ቃል *የልብን አሳብና ፍላጎት ይመረምራል።* ይህ አዎንታዊም አሉታዊም ውጤት አለው። በአዎንታዊ መልኩ፥ የእግዚአብሔር ቃል የተሳሳተ አሳብ መጠንሰስ የጀመርንበትን ስፍራ ያሳየናል። የተሳሳተ ተግባር የሚከተለው ከዚሁ አሳብ ነውና። ይህ ደግሞ የምንለወጥበትን፥ ንስሐ የምንገባበትን፥ ወደ እግዚአብሔር የምንመለስበትንና ወደ እረፍት ከለመግባቱ ፍርድ የምናመልጥበትን መንገድ ያመቻቻል። በአሉታዊ ጎኑ፥ ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ልንደብቅ እንደማንችል ያሳያል። መንፈሳዊ ነን ብለን ሰዎችን ልናሞኝ ብንችልም፥ እግዚአብሔርን ግን ልናታልለው አንችልም። እርሱ በተደበቀው ማንነታችን፥ በነፍሳችንና በአእምሮአችን ያለውን ሁሉ ያያል። በሚያየውም መሠረት፥ ተጠያቂዎች አድርጎ ይፈርድብናል። ይህም በአመዛኙ በውጫዊ ማንነታችን ውስጥ ከሚታየው የበለጠ ነው። ከዛ ትንሺን አለመታዘዝ ወይም ሰዎችን የምትጎዳ የማትመስለውን አነስተኛ ኃጢአት ያያል።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የማይጠሙ በሚመስሉበት ዘመን ውስጥ እንኖራለን፤ አስደናቂ ነገሮችን ለማየት እንናፍቃለን፤ እንደ በልሣን መናገር፥ ፈውስ እና እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች የሚናገሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብቻ እናነባለን፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቁጣ ለማምለጥ፥ እንደ ግለሰቦች እና ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንድንገባ ወደሚፈልገው እረፍት ለመግባት ከፈለግን፥ ሰይፉን ከሕይወታችንና ከአብያተ ክርስቲያኖቻችን ማዛመድ ይኖርብናል። እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ የተደበቀውን እንዲገልጥና እያጠፋን ያለውን በሽታ እንዲያስወግድ መፍቀድ አለብን።

32ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በብዙ ክርስቲያኖች እና አብያተ ክርስቲያናት ልቦች ውስጥ የተሰወሩትን አንዳንድ በሽታዎች ዘርዝር። ለ) እነዚህን ነገሮች ቆፍሮ ለማውጣትና ሰዎችን ለመለወጥ ብቃት ያለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ የሆነበትን ሁኔታ ግለጽ። ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ይህ የእግዚአብሔር ሰይፍ ከሰዎች ሕይወት ኃጢአትን እንዲያስወግድ በተሻለ ሁኔታ የምትጠቀምበት እንዴት ነው ነው? መ) መንፈስ ቅዱስ ሰይፍ ውስጣዊ ሁኔታን ለራስህ እንዲያሳይህ በግል ሕይወትህ ምን እያደረግክ

ነው? ሠ) እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ሰው ትሆን ዘንድ በታላቅ ሰይፉ እንዲያስተካክልህ በጸሎት ጠይቀው።

## አራተኛ ቀን፤ ለሳምንታዊ ስብሰባ ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ክልስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ጥያቄዎች፦

1. ሀ) ጳውሎስ የፊልሞናን መልእክት የጻፈልን ለምንድን ነው? ለ) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጳውሎስና ሌሎችም ጸሐፊዎች በባሪያ አሳዳሪነት ሥርአት ላይ ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው? ሐ) ክርስቶስ ማኅበረሰቡ ያገለላቸውን ሰዎች እንዴት ይመለከት ነበር? (ሉቃስ 5፡29-32 አንብብ።) መ) በኢትዮጵያ ውስጥ ማኅበረሰቡ ያገለላቸውን የሕዝብ ቡድኖች ዘርዝር። ሠ) ክርስቶስ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢኖር ኖሮ ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት የሚያደርግ ይመስልሃል? እንዴት ያስተናግዳቸዋል? ረ) ክርስቶስ ሕዝቡ እነዚህን ሰዎች እንዴት እንዲያስተናግዱ ይጠብቃል? ሰ) ክርስቶስ እነዚህን ኅብረተሰቡ ያገለላቸውን ሰዎች እንድናስተናግድ የሚፈልግበትን መንገድ አሁን እየተስተናገዱ ካሉበት ሁኔታ ጋር አነጻጽር። ዛሬ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) የሚፈልገውን ዓይነት ተግባር እንድናከናውን የቤተ ክርስቲያን ግንዛቤና ልምምድ እንዴት ሊለወጥ ይገባል?

2. ሀ) የዕብራውያን መልእክት የተጻፈበት ዓላማ ምን ነበር? ለ) እነዚህ ሁለቱ ትምህርቶች ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው? ሐ) ከክርስቶስ የሚገኘውን በረከት ያህል ታላቅ ሳይሆኑ ነገር ግን ዛሬ ክርስቲያኖችን እየማረኩ ያሉ የሚመስሉ አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) ክርስቲያኖች በእነዚህ ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረጋቸው እግዚአብሔር ለሕይወታቸው የሚፈልገውና ታላቅ ዘላለማዊ በረከቶችን ከሚያመጡላቸው ነገሮች ሲርቁ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ሠ) በኢትዮጵያ ብዙ አማኞች እምነታቸውን የካዱት ለምንድን ነው? ረ) እነዚህ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ውሳኔዎች ስለሚያስከትሉባቸው ዘላለማዊ ውጤቶች የዘነጉት ነገር ምንድን ነው? ሰ) ክርስቲያኖች በችኮላ እምነታቸውን እንዳይክዱ ቤተ ክርስቲያን እንዴት በተሻለ ሁኔታ ልታስተምር ትችላለች?

3. ሀ) የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት፥ መላእክት፥ ሙሴ እና ኢያሱ እንደሚበልጥ ያሳያል? ለ) የኦርቶዶክስና ወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ከሚኖራቸው ግላዊ ግንኙነት ይልቅ በትውፊቶች እና በቤተ እምነታዊ ውርሶቻቸው ላይ ትኩረት ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያናችን አባሎች ትውፊቶች ላይ እንደማይደገፉና ከክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ምን ልናደርግ እንችላለን?

4. ሀ) የዕብራውያን መልእክት ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያሳየን እንዴት ነው? ለ) ፍጹም ሰው መሆኑንስ እንዴት ያሳያል? ሐ) ክርስቶስ ፍጹም ሰው በመሆኑ ምን ጥቅም እንደምናገኝ ጸሐፊው ምን

ይላል? መ) ክርስቲያኖች የሚጋፈጧቸውና የሚያስፈሯቸው እንዲሁም እምነታቸውን እንዲክዱ የሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ሠ) ክርስቶስ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንዳለፈ ግለጽ። ረ) ዛሬ በምድር ላይ የምንጋፈጣቸውን ችግሮች ያለፈና አሁን በሰማይ ሆኖ ሊረዳን የሚፈልግ ክርስቶስን ማወቅ የሚያበረታታን እንዴት ነው?

5. ሀ) አይሁዶች፥ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን እረፍት ያጡት እንዴት ነው? ለ) እኛም እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን እረፍት ልናጣ የምንችለው እንዴት ነው? ሐ) አንተ ስለምታውቀውና እምነቱን ስለካደ ሰው አስብ። ይህ ሰው እምነቱን ባለመጠበቁ ውድቀቱ ቀስ በቀስ መከሰት የጀመረው እንዴት ነው? መ) ባለማመን እንዳንወድቅ ምን ልናደርግ እንችላለን? ሠ) አማኞች ነን የሚሉ ሰዎች ወደ ዓለም ለመመለስ በሚወስኑበት ጊዜ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን እረፍት የሚገፉት እንዴት ነው? ረ) ዘላለማዊ የመንግሥተ ሰማይ እረፍትን በተመለከተ እንዲህ ዓይነት ውሳኔ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?

6. ሀ) የዕብራውያን ጸሐፊ ከእምነታችን እንዳንወድቅ ወይም ደኅንነታችንን እንዳንተው የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ይረዳናል ይላል? ለ) በብዙ ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲያናት ልቦች ውስጥ የመሠጉትን አንዳንድ በሽታዎች ዘርዝር። ሐ) እነዚህን ነገሮች ቆፍሮ በማውጣት ሰዎችን ሊረዳ የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል አብራራ። መ) ቤተ ክርስቲያንህ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ያለውን ኃጢአት ለማስወገድ ይህንን ሰይፍ እንዴት በተሻለ ሁኔታ ልትጠቀም ትችላለች?